# ክፍል ሁለት

## አረኛው

## ምዕራፍ 17

# የእረኛው ሦስት ግቦች

1. እያንዳንዱ እረኛ መልካም እረኛ ለመሆን መመኘት አለበት፡፡

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።»

ዮሐንስ 10፡11

ሀ. እረኝነትህ የኢየሱስን የእረኝነት ስልት የተከተለ ከሆነ አንተ መልካም እረኛ ነህ፡፡

ለ. የመጋቢነት ሥራህ የኢየሱስን ከመሰለና ፍሬህም ከእርሱ ፍሬ ጋር ከተመሳሰለ አንተ መልካም እረኛ ነህ::

2. እያንዳንዱ እረኛ ታላቅ እረኛ ለመሆን መመኘት አለበት፡፡

«በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ...»

ዕብራውያን 13፡20

ሀ. እንደ እረኛ የሚገባውን ያህል እውቀትና ክህሎት ከተቀበልህ ታላቅ እረኛ ነህ፡፡

ለ. በርካታ ቁጥር ያላቸው በጎች በሥርህ ካሉ አንተ ታላቅ እረኛ ነህ፡፡

ሐ. ለበርካታ አመታት በተሳካ ሁኔታ የመጋቢነት አገልግሎትህን ከፈጸምክ አንተ ታላቅ እረኛ ነህ፡፡

3. እያንዳንዱ እረኛ የእረኞች አለቃ ለመሆን መመኘት አለበት፡፡

«የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።»

1ኛ ጴጥሮስ 5፡4

ሌሎች እረኞች በሥርህ ካሉ አንተ የእረኞች አለቃ ነህ፡፡ የእረኞች አለቃ ማለት የሌሎች እረኞች የበላይ ጠባቂ መሆን ማለት ነው፡፡

## ምዕራፍ 18

# በበሩ ያልገቡትን በጎች እንዴት መለየት ይቻላል?

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤»

ዮሐንስ 10፡1

1. **ወደ አገልግሎት መግባት በእግዚብሔር ጥሪ መሆን አለበት። ወደ አገልግሎት መግቢያ በሩ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው።**

«እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።»

ዕብራውያን 5፡4

መለኮታዊ ጥሪ ከሌለህ በስተቀር ወደ አገልግሎት መግባት የለብህም። ለአገልግሎት እንድትለይ ጥሪ እንዳለህ በግልህ እርግጠኛ መሆን አለብህ።

ለአገልግሎት ያለህ ጥሪ የአገልግሎትህ መሠረት ነው። በአገልግሎትህ የምታከናውነው ነገር ሁሉ የሚመሠረተው በጥሪህ ላይ ነው።

2. **ወደ አገልግሎት የሚያስገባው በር ወደ ሌሎች ሙያዎች ከሚያስገባው በር የተለየ ነው።**

ወደ ህክምና ሙያ መግቢያ በሩ ከህክምና ተቋም መመረቅ ነው። ወደ ህግ ሙያ መግቢያ በሩ ከህግ ተቋም መመረቅ ነው። ወደ ሂሳብ ሙያ መግቢያ በሩ የሂሳብ አያያዝ ሠርተፊኬት መያዝ ነው። ነገር ግን ወደ አገልግሎት መግቢያ በሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤትን ጨምሮ ከየትኛውም ት/ቤት መመረቅ አይደለም። ወደ አገልግሎት የሚያስገባው በር መለኮታዊ ጥሪ በመቀበልና ለጥሪው በመታዘዝ ነው።

3. ያለ ጥሪ ወደ አገልግሎት የገቡ ሰዎች የሚያስከትሉት ውጤት የሌባና የዘራፊ ውጤት አይነት ነው፡፡

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩየማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤»

ዮሐንስ 10፥1

እስኪ በርካታ የህክምና ዶክተር ያልሆኑ ሰዎች የህክምና ዶክተር እንደሆኑ ሲያስመስሉ አስብ፡፡ የፋርማሲ ሙያ የሌላቸው ሰዎች በሚያስራጩት የተሳሳተ መድሀኒት ንጹሀንን ሲፈጁ ይታይሀ፡፡ እነኚህን ሰዎች ሌቦች፣ ወንበዴዎች ወይም ነፍሰ ገዳዮች ብላችሁ ብትጠሯቸው አትሳሳቱም፡፡ በምርጫ ያላሸነፈ ፕሬዚዳንት ሲመራ ይታያችሁ፡፡ ሁሉም ሌባና ዘራፊ እያለ ይጠራዋል፤ በእርግጥም ደግሞ ምርጫውን አጭበርብሯልና ስሙ ይገባዋል፡፡

አንድ ሰው ያለ ጥሪ ወደ አግልግሎት ለመግባት በሚሞክርበት ጊዜ ሌባና ወንበዴ ሆነ ማለት ነው፡፡ የማይገባውን ሥፍራ ስለያዘ ያ ሌባ ያሰኘዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች በአገልግሎት ውስጥ መገኘት ነው ከውጭ ለሚመለከቱ ግራ መጋባትን የሚፈጥረው፡፡

በርካታ ‹‹የተከበሩ አገልጋዮች›› ያልተጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በእርግጥም ሌቦችና ዘራፊዎቹ እንደ እውነተኛ እረኞችና መጋቢዎችአንድ አይነት ልብስ ለብሰው ጎን ለጎን ቆመዋል፡፡ ጌታ ምህረቱን ያውርድልን!

4. ከቤተክርስቲያን ውጭ ታዋቂ ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት ወደ አገልግሎት የሚገቡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ተፈላጊ ሰው ስለሆንክ በቤተክርስቲያንም ተፈላጊ መሆን አለብህ ማለት አይደለም፡፡ ከቤተክርስቲያን ውጭ ያለህ ሥልጣን በቤተክርስቲያንም መሪነትና ሥልጣን ይኖርሃል ማለት አይደለም፡፡ በተጨማሪ፣ ወላጆችህ መጋቢዎች ስለሆኑ በቤተክርስቲያን ላይ ሥልጣን አለህ ማለት አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያንን መምራት የሚቻለው በእግዚአብሔር ጥሪ ነው፡፡

« የሌዊም ልጅ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ ከሮቤልም ልጆች የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ ኦን በሙሴ ላይ ተነሡ።

ከእስራኤልም ልጆች ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ወሰዱ ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ።

በሙሴና በአሮን ላይ ተሰብስበው። ማኅበሩ ሁሉ እያንዳንዳቸው ቅዱሳን ናቸውና፥ እግዚአብሔርም በመካከላቸው ነውና እናንተ እጅግ አብዝታችኋል በእግዚአብሔርም ጉባኤ ላይ ለምን ትታበያላችሁ? አሉ።»

ዘኍልቁ 16፡1-3

5. በሰዎች ተገፋፍተው ወደ አገልግሎት የሚገቡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

ሳዖል ወደ ሥልጣን የመጣው ህዝቡ ንጉሥ ስለፈለገ ነበር። ሰዎች ስለፈለጉህ ብቻ ወደ አገልግሎት መምጣት የለብህም። ወደ አገልግሎት መግባት ያለብህ ከእግዚአብሔር ጥሪ ካለህ መሆን አለበት። የሕዝብ ድምጽ የእግዚአብሔር ድምጽ *አይደለም!* የብዙሀን ድምጽ የእግዚአብሔር ድምጽ አይደለም! ከቤተክርስቲያን ውጭ ያለውን አሰራር እንዳለ ወደ ቤተክርስቲያን በማምጣት እንዳትሳሳት ተጠንቀቅ።

«እነሆ፥ አንተ ሸምግለሃል፥ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን አሉት።

የሚፈርድልንም ንጉሥ ስጠን ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው ። ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው። በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ።»

1ኛ ሳሙኤል 8፡5-7

6. በህዝባዊ አመጽ ወደ አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

እንዲህ ያሉ ሰዎች ወደ ሥልጣን የሚመጡት በኃላፊነት ላይ ያሉትን በመገዳደርና በመንቀፍ ነው። በተሠራው ሥራ ሁሉ ላይ ጥያቄ በማንሳት ግርታንና ጥርጣሬን ይዘራሉ።

« የሌዊም ልጅ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ ከሮቤልም ልጆች የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ አን በሙሴ ላይ ተነሡ። ከእስራኤልም ልጆች ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ወሰዱ ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ። በሙሴና በአሮን ላይ ተሰብስበው። ማኅበሩ ሁሉ እያንዳንዳቸው ቅዱሳን ናቸውና፥ እግዚአብሔርም በመካከላቸው ነውና እናንተ እጅግ አብዝታችኋል በእግዚአብሔርም ጉባኤ ላይ ለምን ትታበያላችሁ? አሉ።»

ዘኍልቁ 16፡1-3

ብዙ መጋቢዎች ወደ አገልግሎት የሚገቡት በአመጽ ነው። በመሪዎች ላይ በሚነሳ ህዝባዊ አመጽ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ አንድ መጋቢ ብቅ ይልና የራሱን ሥራ ይጀምራል። እንዲህ አይነት ሰዎች በኃላፊነት ላይ የነበሩትን መሪዎች በመቃወም ወደ አገልግሎት እንደገባው እንደ ቆሬ ናቸው። እነኚህ ሰዎች ምንም የአገልግሎት መሠረት የሌላቸው ለጥፋት የተመደቡ ናቸው። መጨረሻቸውም እንደ ቆሬ መጨረሻ ይሆናል! ቀስ በቀስም ይጠፋሉ! በትክክለኛ መንገድ ወደ አገልግሎት ስላልመጡ በአገልግሎታቸው አይጸኑም። በኃላፊነት ላይ ካሉ መሪዎች ጋር መጋጨት በተሳሳተ መንገድ ወደ አገልግሎት መግባት ነው።

አንዳንድ መጋቢዎች ከእኔ ጋር በመጋጨት ወደ አገልግሎት ሲገቡ ተመልክቻለሁ። ይተቹኝና አመራሬን በተመለከተ የንጹህን አባላትን ህሊና ይመርዙ ነበር። በፕሮፓጋንዳቸው ተከታዮችን በማፍራት የራሳቸውን አገልግሎት ጀመሩ።

ሆኖም ግን አንድ ሰው መሠረት ሳይኖረው ምን ሊያደርግ ይችላል? ሞኝ ብቻ ነው ቤቱን በትችት፣በኃሜትና ስም በማጥፋት አሸዋ ላይ የሚሰራ! ቤትህን በአለቱ ላይ መስራት አለብህ። ዐለቱ የእግዚአብሔር ቃል ነው! ዐለቱ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው! ቤታቸውን በአሸዋ ላይ የሰሩ ሁሉ ቤቶቻቸው በላያቸው ላይ ሲወድቅ ማየታቸው አይቀርም።

7. ወደ አገልግሎት መጥተው የተሰጣቸውን በእግዚአብሔር ቤት የማገልገል ዕድል ዋጋ የማይሰጡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

እነዚህ ሰዎች አለቅጥ ደፋሮች እና አመራሩን እና የሥልጣን መዋቅሩን ከቁብ የማይቆጥሩ ናቸው። ከገደብ አልፈው ስለማይመለከታቸው ነገር ይናገራሉ። አለቅጥ ደፋሮች በመሆናቸው ያልተሰጣቸው የክብር ስፍራ ላይ ለመቀመጥ ወደኋላ አይሉም። የእግዚአብሔር ጥሪ ‹‹ያን ያህል ትልቅ ነገር›› እንዳይደለ የሚያስቡ እና መጋቢ መሆንም የተለየ ነገር አይደለም የሚሉ ደፋር ሰዎች ናቸው። እነኚህ ሰዎች በእነርሱና በቤተክርስቲያን መሪዎች መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ያስባሉ። *በልባቸውም መጋቢውን ‹‹ እኔም እንዳንተ መሆን እችላለሁ፣ ‹‹አንተ የምታደርገውን እኔም ማድረግ እችላለሁ።›› ይላሉ።* የተከበሩ አገልጋዮች ለመሆን ከመፈለጋቸውም በላይ ከሌሎች የተከበሩ አገልጋዮች ጋር እኩል እንደሆኑ ያወራሉ።

ይህ ሰዎች ወዳልተጠሩበት አገልግሎት እንዲገቡ የሚያደርግ አደገኛ ባህሪና ደፋርነት ነው።

«ሙሴም ቆሬን አለው። እናንተ የሌዊ ልጆች፥ ስሙ የእስራኤል አምላክ ከእስራኤል ማኅበር የለያችሁ፥ የእግዚአብሔርንም ማደሪያ አገልግሎት ትሠሩ ዘንድ፥ እንድታገለግሉአቸውም በማኅበሩ ፊት ትቆሙ ዘንድ ወደ እርሱ ያቀረባችሁ አይበቃችሁምን? አንተን ከአንተም ጋር የሌዊን ልጆች ወንድሞችህን ሁሉ ወደ እርሱ አቅርቦአል ክህነትንም ደግሞ ትፈልጋላችሁን?»

ዘኍልቁ 16፡8-10

8. በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሳውን ማጉረምረም እንደ ዕድል በመጠቀም ወደ አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

ያልበሰሉና ልምድ የሌላቸው ሰዎች አለመብቃታቸውን በማጉረምረም ለመሸፈን ይሞክራሉ። ብዙ ሰዎች ያጉረመረሙበት ጉዳይ አንዳች ትክክል ነገር ቢኖረው ነው ብለው ይነሳሉ። ሀሳባቸው መልካም ይመስላል፤ ፃድቅ የመሆን ስሜትም ያጎናፅፋል። ያም ሆኖ ግን ሀሳቡ የተሳሳተ ነው። የትኛውም የሹክሹክታ ውይይት እና አጠቃላይ ሐሜት ስለ ምንም ነገር የልብ ልብ እንዲሰማህ እንዲያደርግ አትፍቀድ። ለምታደርገው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር ጥሪ በራሳቸው በቂ መሠረቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ዐለት ነው። የሰዎች ማጉረምረም ደግሞ አሸዋ ነው። ቤትህን በአሸዋ ላይ አትስራ። ቤትህን በዐለቱ ላይ ሥራ!

«የሌዊም ልጅ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ ከሮቤልም ልጆች የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ አን በሙሴ ላይ ተነሡ። ከእስራኤልም ልጆች ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ወሰዱ ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ። በሙሴና በአሮን ላይ ተሰብስበው...»

ዘኍልቁ 16፡1-3

9. በዙሪያቸው በሰበሰቧቸው አመጸኛ ሰዎች ስም እና ትልቅነት በመተማመን ወደ አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

አለመታደል ሆኖ ሰዎች በውጪያዊ ሀብትና ሥልጣን ይመሰጣሉ። የሰዎች ጉራና ውጪያዊ ማንነት ለአገልግሎት ዋጋ ያለው ይመስላቸዋል። ሰዎችን የሚያማልል ባህሪ፤ ውድ መኪናዎች፤

ገንዘብን በየቦታው መርጨትና ስለ ራስ ታላቅነት በየቦታው ማወጅ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሊተካ አይችልም። የእግዚአብሔር ጸጋ የጎደላቸው አመጸኛ ሰዎች ድፍረታቸውን ለማጎልበት እነዚህን ነገሮች በማድረግ መርገጥ በማይገባቸው ሥፍራ መራመድ ይጀምራሉ።

> « የሌዊም ልጅ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ ከሮቤልም ልጆች የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ አን በሙሴ ላይ ተነሡ። ከእስራኤልም ልጆች ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ወሰዱ ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ። በሙሴና በአሮን ላይ ተሰብስበው...»
>
> ዘኍልቁ 16፡1-3

10. ሳይላኩ ወደ አገልግሎት የሚገቡና ትንቢት የሚናገሩ ሰዎችን ለይተህ እወቅ።

አንዳንድ ሰዎች ወደ አገልግሎት የሚገቡት ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ነው። እግዚአብሔር አልተናገራቸውም ግን ይሮጣሉ! እግዚአብሔር አልላካቸውም ግን ይሄዳሉ! አገልግሎትን እንደ ጥሩ የሥራ ዕድል ይቆጥሩታል።

አንድ ጊዜ በቴሌቪዥን አንድ አገልጋይ ወደ አገልግሎት የገባው በኬሚስትሪ፣ በታሪክ፣ በሂሳብ፣ በባዮሎጂ ወይም በየትኞቹም የቀለም ትምህርት ዓይነቶች ውጤታማ ስላልሆነ እንደሆነ ሲናገር ሰምቻለሁ። ለዚህ ነው ወደ አገልግሎት የመጣው። ሁላችንም እያየን ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እንደተናገረው ያለማፈር በቴሌቪዥን መናገራቸው አያስገርምም? አልተላኩም ግን ሄደዋል! እግዚአብሔር አልተናገራቸውም ነገር ግን ትንቢት ይናገራሉ ያስተምራሉ! እንዲህ ያሉትን ሰዎች ለይተህ እወቅ! የእነርሱን አገልግሎት ቁጭ ብለህ አትስማ - የተሳሳቱ ሰዎች ናቸውና!

> «እኔ ሳልልካቸው እነዚህ ነቢያት ሮጡ እኔም ሳልነግራቸው ትንቢትን ተናገሩ።»
>
> ኤርምያስ፡ 23፡21

11. በተሳሳተ ህልም ምክንያት ወደ አገልግሎት የሚገቡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ!

ብዙ ሰዎች የተሳሳተ ህልም ያያሉ። ያለመታደል ሆኖ አንዳንዶቹ ከተሳሳተ ህልም የተነሳ ወደ አገልግሎት ይገባሉ። እንደምትረዱት የተሳሳተ አገልግሎት ሰዎችን ፈጽሞ አይጠቅምም። በህይወታቸው

ሕዝብ እንዲስት በማድረጋቸው እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነቢያትን ረግሟል፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉም አገልጋይ ወደ አገልግሎት ከመግባቱ በፊት ከእግዚአብሔር መስማቱን ይናገራል፡፡ ያለመታደል ሆኖ አንዳንዶች የገዛ ምኞታቸውን ራዕይና ህልም አይተው ነው የመጡት፡ ፡ እነዚህ አገልግሎቶችን ሁሉ ጊዜ እንዲገልጣቸው መተው ነው፤ በፍሬያቸው እናውቃቸዋለን፡፡

> «እነሆ፥ ሐሰትን በሚያልሙ በሚናገሩም በሐሰታቸውና በድፍረታቸውም ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ፥ ይላል እግዚአብሔር እኔም አልላክኋቸውም አላዘዝኋቸውምም ለእነዚህም ሕዝብ በማናቸውም አይረቡአቸውም፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡»
>
> ኤርምያስ 23፡32

12. የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ታላቅነት በመዘንጋት በግዴለሽነት ወደ አገልግሎት የሚገቡትንም ለይተህ እወቃቸው፡፡

ኤርምያስ ሰዎች አገልግሎትን ይዳፈራሉ ሲል ይህን ማለቱ ነው፡፡ አንድ ቀን አንድ የሚያምር መኪና ስነዳ ያየኝ ሰው አስገራሚ አስተያየት ሲሰጥ ሰማሁት፡፡ ‹‹ሁላችንም መጋቢዎች መሆንና ቤተክርስቲያን መትከል አለብን፡፡ ከዚያም እንደዚህ ያለ የሚያምር መኪና ይኖረናል›› አለ፡፡ እግዚአብሔር የዚያን አላዋቂ ሰው ንግግር እንድሰማ አደረገኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ብዙ አላዋቂ ሰዎች በጓዳቸው የሚሉት ነገር ስለሆነ ነው፡፡ ያማረ መኪና ለመንዳት ወደ አገልግሎት መምጣት የሚፈልግ ሰው ካለ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን በግንባሩ በምድር ላይ ሲወድቅ መፈንከቱ ስለማይቀር መጠገኛ ፋሻ እንዲይዝ ምክሬን እለግሳለሁ፡፡

አገልግሎት ቀላል ነገር ስላይደለ ማንም በድፍረት ዘው የሚልበት አይደለም፡፡ ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለመምጣት የሚያመነቱ ሰዎች ላይ ጥበብን አያለሁ፡፡ ጥንቃቄ እያደረጉ እንደሆነ እረዳለሁ፤ ደግሞም አገልግሎት የሚይጠይቀውን ዋጋ በማስተዋል እየተረዱ እንደሆነ ይገባኛል፡፡ አገልግሎትን አቃሎ የሚይዝ ሰው የሚሠራውን የሚያውቅ አይደለም፡፡


> «እነሆ፥ ሐሰትን በሚያልሙ በሚናገሩም በሐሰታቸውና በድፍረታቸውም ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ፥ ይላል እግዚአብሔር እኔም አልላክኋቸውም አላዘዝኋቸውምም ለእነዚህም ሕዝብ በማናቸውም አይረቡአቸውም፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡»
>
> ኤርምያስ 23፡32

13. በውሸትና በማታለል ወደ አገልግሎት የሚመጡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ፡፡

አንዳንድ ሰዎች በውሸትና በማታለል ሳይቀር ወደ አገልግሎት ይመጣሉ፡፡ ጥሪ እንዳላቸው ይናገራሉ ነገር ግን ምንም ዓይነት ጥሪ የላቸውም፡፡ የሚፈልጉት ሥራ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን በግልጽ ከመናገር ይልቅ መንፈሳዊነትን በማላበስ ጥሪ እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ሁሉ ደግሞ በአብዛኛው ውሸትና ግብዝነት ነው፡፡

«እኔ አልላክኋቸውምና ነገር ግን እኔ እንዳሳድዳችሁ፥ እናንተና ትንቢት የሚናገሩላችሁ ነቢያትም እንድትጠፉ በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገራሉ፥ ይላል እግዚአብሔር፡-»

ኤርምያስ 27፡15

14. ሰዎች እውነት ያልሆነን ነገር አምነው እንዲቀበሉ በማድረግ ልዩ ችሎታቸው ወደ አገልግሎት የሚገቡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ፡፡

ሐሰተኛ ነቢያት በኃላፊነት ላይ ያሉ መሪዎችን ይከሳሉ፤ይተቻሉ፡፡ ህዝቡ እወነት ያልሆነ ነገርን እንዲያምን ያደርጋሉ፡፡ መሪዎቻቸውን በክፉ እንዲጠሯቸው ያደርጋሉ፡፡ ሐናኒያ የተባለው ሀሰተኛ ነቢይ በውሸት ስላሳታቸው ህዝቡ ኤርሚያስን የኢየሩሳሌምን ጥፋት የሚተነብይ ክፉ ሰው አድርገው ቆጥረውት ነበር፡፡ ዓለምን በሙሉ መዋሸትና ማታለል የሠይጣን ባህሪ ነው፡፡ የሠይጣን የውሸት አገልጋዮችም ብዙዎች እውነት ያልሆነን ነገር እንዲያምኑ በአስገራሚ ሁኔታ ያስታሉ፡፡

«ነቢዩም ኤርምያስ ነቢዩን ሐናንያን፡- ሐናንያ ሆይ፥ ስማ ይህ ሕዝብ በሐሰት እንዲታመን አድርገሃል እንጂ እግዚአብሔር አልላከህም።»

ኤርምያስ 28፡15

«እግዚአብሔር ስለ ኔሔላማዊው ስለ ሸማያ እንዲህ ይላል ብለህ ወደ ምርኮኞች ሁሉ ላክ። እኔ ሳልልከው ሸማያ ትንቢት ተናግሮላችኋልና፥ በሐሰትም እንድትታመኑ አድርጎአችኋልና»

ኤርምያስ 29፡31

ብዙ ታላላቅና ታዋቂ አገልጋዮች የወንጌል ዋና መልዕክት ያልሆኑ አስተምህሮችን ይሰብካሉ፡፡ ወንጌል ይመስላልነገር ግን ወንጌል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ አይሰኝም፡፡ እንሰብከው ዘንድ

የላከልንን ወንጌል ስለማይሰብኩ እግዚአብሔር በእነርሱም፣ በመልዕክታቸውም አይደሰትም።

ነገር ግን ገንዘብ ወዳድና ሥጋውያን የሆኑ ሰዎች የዚህ ዓይነቱን መልዕክት በሞቅታ ይቀበሉና እንዲዚያ ያለ ስብከት ሰምተው እንደማያውቁ ለመጋቢያቸው ይነግሩታል። ሁኔታው እንዲህ ከሆነ በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ በሀሰተኛ ነቢያት የሚፈጸመው ማታለል የከፋ ነው ማለት ነው። የዘመኑ ሀሰተኛ ነቢያ የስኬትና የብልጽግና ምልክቶች እንዲሁም የህይወትን አረማመድና በዚህ ዓለም የሚሆነውን ነገር ሁሉ ለምን እንደሚሆን የሚያውቁ ‹‹ፈጽሞ ስህተት የማይሰሩ›› መላዕክቶችን ይመስላሉ።

ነገር ግን ልክ እንደ ኢዮብ ሶስቱ አጽናኞች እነኚህ በአንተ ላይ የሚሆነው ነገር ሁሉ ምክንያቱን እናውቃለን የሚሉ መጋቢዎች ብዙ የሚሳሳቱት ነገር አለ። በስተመጨረሻ ኢዮብ ጻድቅ መሆኑና ሶስቱ ወዳጆቹ ደግሞ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ተገልጧል። በፍርድ ቀን ከእነዚህ መጋቢዎች አብዛኛዎቹ ኃጢአተኝነታቸው ይገለጣል።

15. በጨለማው ጉልበት ወደ አገልግሎት የገቡትን ሰዎች ለይተህ እወቅ።

በአንድ ወቅት ያልተለመዱ አስተምህሮዎች ባሏት አንዲት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል መልዕክት አቀረብኩ። በስብከቱ መጨረሻ ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ ጥሪ ሳደርግ ዋናውን መጋቢ ጨምሮ የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢዎች በሙሉ ወደ መድረኩ መጥተው ህይወታቸውን ለክርስቶስ ሰጡ። እነዚህ ሰዎች እንዴት መጋቢዎች ሊሆኑ ቻሉ። እስከዛሬስ በምን ኃይል ነበር ሲያገለግሉ የነበሩት ብሎ የሚጠይቅ ሰው ሊኖር ይችላል። በእርግጥም በጥንቆላና በምናምንቴ ነገር ወደ አገልግሎት የገቡ ሀሰተኛ ነቢያት ያሏቸው ሀሰተኛ አብያተክርስቲያናት አሉ። በእውነተኛ አገልጋይና በሀሰተኛ አገልጋይ መሀከል ያለውን ልዩነት እንዴት ማወቅ ይቻላል?

ይህንና ያንን ብዬ ለማነገር አልችልም። ነገር ግን አንዳንዴ ልብህ የማይቀበለው አገልጋይ ያጋጥምሀል። እግዚአብሔርም እንዲህ ባለው አገልግሎት እንድትሳብ አያደርግህም።

ብዙ ጊዜ ይሄኛው ትክክል ነው ያኛው ደግሞ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል ግልጽ መንገድ የለም። የሰዎች ልብ ማየት ስለማትችል አስተያየት ከመስጠት ተጠንቀቅ። ዝም ብለህ ልብህን አዳምጥ።

ከውጭ በምናየው ነገር እንዳንፈርድ የሚናገረንን የእግዚአብሔር ቃል አስብ። ሐሰተኛ የሚመስሉ ነገር ግን ትክክለኛ አገልግሎቶች አሉ። አብ ያልተከለው ተክል ሁሉ እንደሚነቀል አስተውል።

> «እግዚአብሔር ሳይልካቸው እግዚአብሔር ይላል የሚሉ ሰዎች ከንቱ ነገርንና ውሸተኛ ምዋርትን አይተዋል ቃሉም ይጠና ዘንድ ተስፋ አስደርገዋል።»
>
> ሕዝቅኤል 13፡6

## ምዕራፍ 19

# የእረኝነት ተግባራት

## ገርና ርህሩህ መሆን

### ገርና ርህሩህ የመሆን አምስት ምክንያቶች

1. ልጆች ገሮች ስለሆኑ እረኞች ገሮችና ርህሩህ መሆን አለባቸው።

«እርሱም አለው፦ ጌታዬ ሆይ፥ ልጆቹ ደካሞች እንደ ሆኑ ታውቃለህ በጎችና ላሞችም ግልገሎቻቸውን ያጠባሉ ሰዎችም አንድ ቀን በችኮላ የነዱአቸው እንደ ሆነ ከብቶቹ ሁሉ ይሞታሉ።»

ዘፍጥረት 33፡13

2. በመንጋዎቻቸው መካከል ታናናሾች ስለሚገኙ እረኞች ገሮችና ርህሩሆች መሆን አለባቸው።

«እርሱም አለው፦ ጌታዬ ሆይ፥ ልጆቹ ደካሞች እንደ ሆኑ ታውቃለህ በጎችና ላሞችም ግልገሎቻቸውን ያጠባሉ ሰዎችም አንድ ቀን በችኮላ የነዱአቸው እንደ ሆነ ከብቶቹ ሁሉ ይሞታሉ።»

ዘፍጥረት 33፡13

3. በችኮላ ከተነዱ መንጋው በሙሉ ስለ ሚያልቅ እረኞች ገርና ርህሩህ መሆን አለባቸው።

«እርሱም አለው፦ ጌታዬ ሆይ፥ ልጆቹ ደካሞች እንደ ሆኑ ታውቃለህ በጎችና ላሞችም ግልገሎቻቸውን ያጠባሉ ሰዎችም አንድ ቀን በችኮላ የነዱአቸው እንደ ሆነ ከብቶቹ ሁሉ ይሞታሉ።»

ዘፍጥረት 33፡13

4. መንጋው በቀስታ መመራት ስላለበት እረኞች ገሮችና ርህሩሆች መሆን አለባቸው።

«ጌታዬ ከባሪያው ፊት ቀድሞ ይለፍ እኔም ወደ ሴይር ከጌታዬ ዘንድ እስከደርስ ድረስ ከፊቴ ባሉት በእንስሳቱ እርምጃና በሕፃናቱ እርምጃ መጠን በዝግታ እከተላለሁ።»

ዘፍጥረት 33፡14

5. መንጋው በታናናሾች አቅም ልክ መራመድ ስላለበት እረኞች ገሮችና ርህሩሆች መሆን አለባቸው።

«ጌታዬ ከባሪያው ፊት ቀድሞ ይለፍ እኔም ወደ ሴይር ከጌታዬ ዘንድ እስክደርስ ድረስ ከፊቴ ባሉት በእንስሳቱ እርምጃና በሕፃናቱ እርምጃ መጠን በዝግታ እከተላለሁ።»

ዘፍጥረት 33፡14

*ምዕራፍ 20*

# የእረኝነት ተግባራት

## አቅጣጫ ማሳየትና መምራት

*1. እረኛ በጎቹን ወደ እረፍት ውሃ መምራት አለበት፡፡*

«በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።»

መዝሙር 23፡2

*2. እረኛ በጎቹን ወደ ለመለመ መስክ መምራት አለበት፡፡*

«በለመለመ መስክ ያሳድረኛል ...»

መዝሙር 23፡2

*3. በምድረ በዳ ውስጥ እረኛ በጎቹን ሊመራቸው ይገባል፡፡*

«ሕዝቡን ግን እንደ በጎች አሰማራቸው፥ እንደ መንጋም በምድረ በዳ መራቸው። በተስፋም መራቸው አልፈሩምም፥ ጠላቶቻቸውንም ባሕር ደፈናቸው። ወደ መቅደሱም ተራራ አገባቸው፥ ቀኙ ወደ ፈጠረችው ወደዚህች ተራራ»

መዝሙር 78፡ 52-54

*4. እረኛ ህዝቡን እንደ መንጋ በጋራ መምራት መቻል አለበት፡፡*

ህዝብን በጋራ መምራት የተለያየ አመለካከት፣ ልምድና አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች ለመምራት የሚያስችል መርሆዎችን መከተል ማለት ነው፡፡የእረኝነት ጥበብ የሚቃወሙ፣ አስተያየት የሚሰጡ እና አመፀኛ በጎች ያሉበትን ስብስብ የመምራት ጥበብ ነው፡፡ እያንዳንዱን በግል ለማገኘት የማትችለውን በርካታ ቁጥር ያለውን ህዝብ የመምራት ችሎታ ነው፡፡

«በሙሴና በአሮን እጅ ሕዝብህን እንደ በጎች መራሃቸው።»

መዝሙር 77፡20

*ምዕራፍ 21*

# የእረኝነት ተግባራት

## በጎችን መጠበቅ

## እረኞች ለበጎች ሊተጉላቸው የሚገባቸው አምስት መንገዶች

1. *እረኞች ለበጎች ነፍስ፣አዕምሮና ልብ ሊጠነቀቅ ይገባል።* ምናልባት ገበሬ ብትሆን ኖሮ እግዚአብሔር ለሰጠህ መንጋ ውስጣዊ ማንነት የመጠንቀቅን አስፈላጊነት በሚገባ ትረዳ ነበር። እረኛ መሆን ገበሬ መሆን ማለት ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ገበሬ ገንዘብ አጠራቅሞ ከተፈለፈሉ የአንድ ቀን እድሜ ያላቸውን ጫጩቶች ለዶሮ እርባታው እንደገዛ አጫውቶኛል። ‹‹እነኛን ከተፈለፈሉ አንድ ቀን የሆናቸውን ጫጩቶች ገዝቼ እንዲያድጉልኝ ያለመታከት እመግባቸውና እጠነቀቅላቸው ነበር፣ ነገር ግን አላድግ አሉ!።›› ብሎ ነገረኝ።

ይህ ምስኪን ገበሬ ያላወቀው ነገር ቢኖር ጫጩቶቹ በተፈጥሯቸው ችግር እንዳለባቸው ነው። የገዛቸው ጫጩቶች የማደግ አቅም የሌላቸው ነበሩ። የጫጩቶቹ ‹‹ነፍስ›› ላይ ችግር ነበረ። ትክክለኛው የማደግ ችሎታ የጎደላቸው ‹‹ ጤናማ ያልሆኑ ጫጩቶች›› ነበሩ።

እነኚህ የግብርና ችግሮች አንድ እረኛ ስለበጎቹ ነፍስ፣ አዕምሮና ልብ ያለማቋረጥ እንዲተጋ የሚያርጉት ጉዳዮች ናቸው። ውሳጣዊ ችግር ይኖርባቸው እንደሆን ብሎ ይከታተላል። በጎች እንዳያድጉ የሚከለክላቸው ውሳጣዊ የሆነ ችግር ነው።

ሌላ ገበሬ ደግሞ ሊያሳድጋቸው የትኛውንም ጥረት ቢያደርግም አሳማዎቹ አላድግ እንዳሉት አጫውቶኛል። እረኞች ስለበጎቹ ነፍስ፣ አእምሮ እና ልብ ሁልጊዜ መጠንቀቅ የሚገባው፣ ግብርና እንዲህ ዓይነት ችግሮች ስላሉበት ነው። በውስጠኛው ማንነት

ውስጥ ችግር እንዳለ ጠለቅ አድርጎ ይመለከታል፡፡ በጎችን ከማደግ የሚከለክላቸው ውስጣዊ ችግር ነው፡፡

«ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።»

ዕብራውያን 13፡17

2. *እረኞች ስለበጎቻቸው ሀልውና መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ሠይጣን የቤተክርስቲያን አባሎችህን ሊገድልም ይፈልጋል፡፡* የበጎቹ ደህንነት እንዲጠበቅ መጸለይ የመጋቢው ተግባር ነው፡፡ በአንተ ጸሎት ምክንያት እግዚአብሔር ህይወታቸውን ይታደጋል፡፡

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።

ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።

ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ።»

የሐዋሪያት ሥራ 20፡28-31

3. *እረኞች ዘወትር በጸሎትና በምስጋና ውስጥ በመሆን ለበጎቻቸው መጠንቀቅ አለባቸው፡፡*

«ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ።»

ቆላስይስ 4፡2

4. *እረኞች በሌሊት እየተነሱ በመጸለይ ለበጎቻቸው ነፍስ ሊተጉ ይገባል፡፡* በሌሊት ተነስቶ መጸለይ ‹‹ተግቶ መጸለይ›› ይባላል፡፡ ኢየሱስ ትጉና ጸልዩ ብሎ አዘናል፡፡ ተግቶ መጸለይ በሌሊትም እግዚአብሔርን መጠበቅ ማለት ነው፡፡

«እንግዲያስ እንንቃ፤ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ፡፡»

1ኛ ተሰሎንቄ 5፡6

5. *ጠላትን በመቆጣጠር እረኞች ለበጎች ሊተጉላቸው ይገባል፡፡* ሁልጊዜ በጎችን የመንጠቅ የጠላት ሙከራ አለ፡፡ ዶሮ ያረባ የነበረ አንድ ወንድም አስታውሳለሁ፡፡ አንድ ምሽት ድመት ወደ

ዶሮዎቹ ቆጥ ገብቶ ብዙ ጫጩቶችን ገደለ። በግልጽ እንደሚታወቀው ድመት በአንድ ጊዜ ከአንድ ጫጩት በላይ አይበላም። ነገር ግን እሱ ሃምሳዎቹን ገድሎ አረፈው። ይህ የደክምነበትን ለማጥፋት የሚመጣ የጠላት ክፋት ነው። ዲያቢሎስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ማለፉን በሚያጠናቅቅበት ሰዓት ላይ ሰዎች ሳያውቁት ተመልሰው የቤተክርስቲያን አካል ሆነው መቀጠል እስከማይችሉ ድረስ ተጎድተው ይገኛሉ።

**«አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።»**

**2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡5**

*ምዕራፍ 22*

# ጠባቂው እረኛ ያህዌ

## የእረኞች ጥበቃ

1. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች ከጥቃት በመከላከል በጎቻቸውን ሊጠብቁ ይገባል፡፡* እግዚአብሔር በጎቹን በእረኞች በኩል ይጠብቃል፡፡

«እግዚአብሔር የጽድቅ ጋሻዬ ነው፤ ልበ ቅኖችን የሚያድናቸው።»

መዝሙር 7፡10

«እኔ ግን ለኃይልህ እቀኛለሁ፤ በምሕረትህም ማልዶ ደስ ይለኛል፤ በመከራዬ ቀን መጠጊያዬና አምባዬ ሆነኸኛልና፡፡»

መዝሙር 59፡16

«እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና፤ እርሱ መጠጊያዬ ነው አልታወከም።»

መዝሙር 62፡6

«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል፤ እነርሱም ይበሉአቸዋል፤ የወንጭፉንም ድንጋዮች ይረግጣሉ፤ እንደ ወይን ጠጅም ይጠጡአቸዋል፤ እንደ ጥዋዎችም እንደ መሠዊያም ማዕዘኖች የተሞሉ ይሆናሉ።»

ዘካርያስ 9፡15

2. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች ለበጎቻቸው ጠባቂዎች በመሆን ሊጠብቋቸው ይገባል፡፡* እረኞች የበጎቻቸውን ህይወት ያረጋጋሉ፡፡ ታላቁ እረኛ ያህዌም የበጎች ጠባቂ ነው፡፡ ህይወታቸውን ያረጋጋል እግራቸውም አይሰናከልም፡፡

«እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህም አይተኛም።»

መዝሙር 121፡3

3. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች በጎቻቸውን ከዚህ እግዚአብሔርን ከማይፈራ ትውልድ ተጽዕኖ ሊጠብቋቸው ይገባል፡፡* መልካሙ እረኛ ያህዌ በጎቹን ከዚህ ትውልድ ተጽዕኖ

ይጠብቃል፡፡ እረኞች በጎቻቸውን ከትውልዳቸው ተጽዕኖ ይጠብቃሉ፡፡

«አቤቱ፥ አንተ ጠብቀን፥ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን።»

መዝሙር 12፡7

4. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች በጎቻቸውን ከትዕቢት መጠበቅ አለባቸው፡፡* መልካሙ እረኛ ያህዌ በጎቹን ከትዕቢት ይጠብቃል፡፡ እረኞች በእግዚአብሔር ፊት ሰው ምንም እንዳይደለ በማስረዳት ትሕትናን በመስበክና በማስተማር በጎችን ከትዕቢት መጠበቅ ይችላሉ፡፡

«በፊትህ መጋረጃ ከሰው ክርክር ትጋርዳቸዋለህ፥ በድንኳንህም ከአንደበት ክርክር ትሸፍናቸዋለህ።»

መዝሙር 31፡20

5. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች ለበጎቻቸው በመገኘት ሊጠብቋቸው ይገባል፡፡* በጎች ሁልጊዜ እረኞቻውን የት እንደሚያገኙት ማወቅ አለባቸው፡፡ አስተማማኝ የሆነው ያህዌ የሚመኩበትና ወደ ላይ ለሚመለከት ሁሉ የሚገኝ እረኛ ነው፡፡ እረኞች አስተማማኝ ናቸው፤ በጎቻቸውም ይመኩባቸዋል፡፡

«ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ?
ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።
እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም።»

መዝሙር 121፡ 1-3

6. *እንደ ታላቁ እረኛ እንደ ያህዌ መጋቢዎች በጎቻቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ሊጠብቋቸው ይገባል፡፡* ኢየሱስ ይጠብቃቸው ዘንድ በጎቹን ሁሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ፡፡ የቤተክርስቲያን እረኞችም የክርስቶስን ፍለጋ በመከተል በጎቻቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው መስጠት አለባቸው፡፡

«ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።»

የሐንስ 17፡11

# ምዕራፍ 23

# የእረኝነት ተግባራት

## በጎችን መመገብ

1. *እረኛ በጎቹ በለመለመ መስክ እንዲያድሩና ይመገቡ ዘንድ ገበታን ሊያዘጋጅላቸው ይገባል፡፡* የለመለመ መስክና የእረፍት ውሃ በጎች ዘና ብለው እንዲመገቡ ያደርጋቸዋል፡፡

«እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።
በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።
በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።
ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።»

መዝሙር 23፡ 1-6

2. *እረኛ በጎቹን ሊሰበስብ፣ ሊሸከማቸውና ሊመግባቸው ወደሚችልበት ሥፍራ በቀስታ ሰሊመራቸው ይገባል፡፡* የምትመራውን ህዝብ ለትሰበስብ፣ ልትሸከማቸውና በመንገዳቸው ልትመራቸው ጊዜና ፈቀደኝነቱ ከሌለህ ልትመግባቸው የምትችልበት ዕድል መቼውንም አታገኝም፡፡ የዚህ ዓይነቱን ልብ ካላገኙ በጎች ከእረኛው ምንም ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡

«መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።»

ኢሳይያስ 40፡11

3. *የቤተክርስቲያን እረኛ በጎችን በማስተዋልና በጥበብ መመገብ አለበት፡፡* እግዚአብሔርን ማወቅ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር እና መንፈሳዊ መረዳት የቤተክርስቲያን አባሎችህን ህይወት በከፍተኛ ሁኔታ ይለውጣል፡፡ የቤተክርስቲያን እረኛ በሌሎች መንፈሳዊ ባልሆኑ ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡ

ትምህርቶችን በቤተክርስቲያን ከመስጠት መቆጠብ አለበት። እነዚህ የራሳቸው ቦታ አላቸው እኛ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ልናስተምር ይገባል።

«እንደ ልቤም በግ ጠባቆችን እሰጣችኋለሁ፥ በእውቀትና በማስተዋልም ይጠብቁአችኋል።»

ኤርምያስ 3፡15

## ምዕራፍ 24

# የእረኛነት ተግባራት

## መመለስና መፈወስ

1. እረኞች ለበጎቻቸው የሚጠቅሙ ሐኪሞች ሊሆኑ ይገባል። በእረኞች አማካኝነት ፈውስ ወደ ታመመ አካል መድረስ አለበት።

«እናንተ ግን በሐሰት ለባጮች ናችሁ፤ ሁላችሁ የማትጠቅሙ ባለ መድኃኒቶች ናችሁ።»

ኢዮብ 13፡4

2. እረኞች ያዘኑትን፣ የታሰሩትን፣ ድሆችን፣ እውሮችን እና የተጠቁትን ሰዎች ማከም አለባቸው።

«የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን፣ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፤ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ ፤የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል።»

ሉቃስ 4፡18

3. እረኞች ችግር ያለባቸውን፣ ያልተሳካላቸውንና ጉድለት የሚሰማቸውን ሰዎች መርዳት አለባቸው።

«ኢየሱስም ሰምቶ ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም...»

ማቴዎስ 9፡12

4. እረኞች የበጎችን አዕምሮ፣ልብና ስሜት ማደስ አለባቸው። ነፍስን መመለስ ማለት ትርጉሙ ይኸው ነው።

«ነፍሴን መለሳት፤ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።»

መዝሙር 23፡3

5. እረኞች በጎች በገዛ ኃጢአታቸውና አመፃቸው ያጡትን ነገር መልሰው እንዲያገኙ ሊረዷቸው ይገባል።

«ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው አሁን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን፥ እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ ስለ እኔ ጸልይ አለው። የእግዚአብሔርም ሰው እግዚአብሔርን ለመነ፥ የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች፥ እንደ ቀድሞም ሆነች።»

1ኛ ነገሥት 13፡6

*6. እረኞች ህይወትና ሠላም ለበጎች እንዲመለስ ማድረግ አለባቸው።*

«ኤልሳዕም ልጅዋን ያስነሣላትን ሴት። አንቺ ከቤተ ሰብሽ ጋር ተነሥተሽ ሂጂ፥ በምታገኚውም ስፍራ ተቀመጪ እግዚአብሔር ራብ ጠርቶአል ሰባት ዓመትም በምድር ላይ ይመጣል ብሎ ተናገራት።»

1ኛ ነገሥት 8፡1

«ከዚህም በኋላ ደግሞ እጁን በዓይኑ ላይ ጫነበት፤ አጥርቶም አየና ዳነም፤ ከሩቅም ሳይቀር ሁሉን ተመለከተ።»

ማርቆስ 8፡25

«ሁላቸውንም ዙሪያውን አየና ሰውዬውን። እጅህን ዘርጋ አለው። እርሱም እንዲህ አደረገ፥ እጁም እንደ ሁለተኛይቱ ዳነች።»

ሉቃስ 6፡10

## ምዕራፍ 25

# ደም መጣጭ የቤተክርስቲያን መጋቢዎች

ደም መጣጭ (ቫምፓየር) ምንድን ነው? ደምህን የሚመጥ ፍጡር ነው፤ እርሱ በሕይወት የሚኖረው የአንተን ሕይወት በመምጠጥ ነው። ሕይወትህን፣ ደምሕን ይወስዳል። ያለመታደል ሆኖ አንዳንድ እረኞች ከበጎቻቸው የሚወስዱ እንጂ የሚሰጡ አይደሉም። እረኛ ከሚያረባቸው በጎች ጥቅም ማግኘቱ የታወቀ ነው። ከበጎቹ በሚያገኘው ትሩፋት የሚደሰትበት ቀን ይመጣል። እኔ ግን እየተናገርኩ ያለሁት ስለዚህ አይደለም።

እውነተኛ እረኛ ህይወቱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ በጎቹን ይወዳል። የአገልጋይ ልብ የሌለው መጋቢ ዝም ብሎ በጎቹን ይበዘብዛል።

የዚህ ዓይነቱን እረኛ ነፍሱን ለበጎቹ አሳልፎ ከሚሰጠው እረኛ ጋር አነፃፅረው። መልካም እረኛ ለበጎቹ ብዙ ነገር ይሰጣል። መልካም እረኛ ለበጎቹ ብዙ ነገር ያደርጋል። አንተስ የምትሰጥ ነህ ወይስ የምትቀበል? የሚሰጥ እውነተኛ እረኛ ነው። የምታደርገውን ነገር ሁሉ የምታደርገው ከምታገለግለው ህዝብ ለመውሰድ ብቻ ከሆነ አንተ ደም መጣጭ ነህ።

ብዙ ከቤተክርስቲያን ውጭ ያሉ መሪዎችም ደም መጣጮች ናቸው። አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በረሀብና በችጋር እየተጠበሰ እነርሱ የህዝቡን ሀብት ዘርፈው በተቀማጠለ ቤተመንግሥት ውስጥ ይኖራሉ፡ ፡ በደም መጣጭ መሪዎች የሚመራን አገር መለየት ቀላል ነው። ዝም ብለህ ዙሪያህን ቃኝ በሥልጣን ላይ ያሉ ነገሥታት እንዴት የብዙሁኑን ህይወትና ሀብት እየነጠቁ እንዳሉ ታያለህ።

እስራኤላዊያን ንጉሥ እንግሥልን ባሉ ጊዜ እግዚአብሔር የንጉሥ ወግ ምን እንደሚሆን ነገራቸው። የሚነግሠው ንጉሥ ከህዝቡ ብዙ ነገሮችን ይወስዳል። መሪያቸው ይሆናል ነገር ግን ደግሞ የእነርሱን ነገር ሁሉ ይቀማል። እግዚአብሔር ደም መጣጮቹ ሳይመጡ በፊት ህዝቡን አስጠንቅቆ ነበር። የቤተክርስቲያን እረኛ ስትሆን የበጎችህን

ህይወት የምትበዘብዝ ‹‹ ደም መጣጭ መጋቢ›› ትሆናለህን? ወይስ እንደ ኢየሱስ የማይተካ ህይወትን ለበጎችህ አሳልፈህ ትሰጣለህ?

1. ደም መጣጭ እረኛ ልጆችህን ወስዶ ባሪያዎች ያደርጋቸዋል፡፡ ወደተሻለ እንዲያድጉ ከመርዳት ይልቅ በእነርሱ ይጠቀማል፡፡ ደም መጣጭ መጋቢ ልጆችህን የራሱ ያደርጋቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ወዳንተ ለሚልካቸው ልጆች ምን የምትሰጣቸው ነገር አለህ?

ሳሙኤልም የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ንጉሥን ለፈለጉ ሕዝብ ነገራቸው። እንዲህም አለ፦ "በእናንተ ላይ የሚነግሠው የንጉሥ ወግ ይህ ነው፤ ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሰረገለኞችና ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፥ በሰረገሎቹም ፊት ይሮጣሉ፡፡"

1ኛ ሳሙኤል 8፡10-11

2. ደም መጣጭ መጋቢዎች እየሙህክ ልጆችህን ይነጥቁሀል፡፡ ለልጆቹ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ያለህን ለእነርሱ እድገት ታፈሳለህ ወይስ ከእነርሱ ትወስዳለህ? ደም መጣጭ መጋቢ የወጣቶችን አስፈላጊነት አይረዳም፡፡ ተረካቢ ትውልድ መሆናቸው አይታየውም፡፡ የመጪው ትውልድ መሪዎች መሆናቸውን አያስተውልም፡፡

ሳሙኤልም የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ንጉሥን ለፈለጉ ሕዝብ ነገራቸው። እንዲህም አለ፦ "በእናንተ ላይ የሚነግሠው የንጉሥ ወግ ይህ ነው ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሰረገለኞችና ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፥ በሰረገሎቹም ፊት ይሮጣሉ፡፡"

"በዚያም ቀን ለእናንተ ከመረጣችሁት ከንጉሣችሁ የተነሣ ትጮኻላችሁ፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር አይሰማችሁም።"

1ኛ ሳሙኤል 8፡10-11፣18

3. ደም መጣጭ መጋቢዎች ሴት ልጆችህን ወስደው ያጎሳቁሏቸዋል፡፡ ለሴት ልጆችህ ምን ታደርጋለህ? ከእነሱ ትነጥቃለህ ወይስ ለእነርሱ ትሰጣለህ? ደም መጣጭ መጋቢ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ወጣት ሴት ልጆች መጠቀሚያ ለማድረግ ነው የሚያስበው፡፡ በሴት ልጆች ውስጥ ያለውን የመስራት አቅም ማየት አትችልምን? የወደፊቱ ሴት መጋቢዎችና ዘማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን ደስ ልትሰኝባቸው ትችላለህ፡፡

"ሴቶች ልጆቻችሁንም ወስዶ ሽቶ ቀማሚዎችና ወጥቤቶች፣ አበዛዎችም ያደርጋቸዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 8፡13

4. ደም መጣጭ መጋቢ እያስለቀሰህ እርሻዎችህን ይወስዳል። ስለ አባላቶችህ እርሻና ንግድ ምን ማድረግ ትችላለህ? የበለጠ እንዲበለጽጉ ልትረዳቸው ትችላለህን? የንግድ ግንኙነት ታመቻችላቸዋለህን? እነርሱን ለመርዳት ልትሰጣቸው የምትችው ነገር አለህን? ነው ወይስ ከእነርሱ ትወስዳለህ? እውነተኛ መጋቢ ግን የአባላቶቹ እርሻና ንግድ እስኪስፋፋ ድረስ ያበረታታቸዋል።

"ከእርሻችሁና ከወይናችሁም መልካም መልካሙን ወስዶ ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 8፡14

5. ደም መጣጭ መጋቢ እያስለቀሰህ የፍሬህንና የወይንህን አንድ አሥረኛ ይወስዳል። ደም መጣጭ መጋቢ አሥራት እየወሰደ ያስለቅስሀል። የሚሰበሰበው አሥራት ምን ላይ እንደዋለ ልታይ ወይም ልታውቅ አትችልም። መልካም መጋቢ አሥራት ሲሰበስብ ደስ ይልሀል። ምክንያቱም ለትክክለኛ ነገር ስለሚውልና በስተመጨረሻም መላው ማህበር ይጠቀማል።

"ከዘራችሁና ከወይናችሁም አሥራት ወስዶ ለጃንደረቦቹና ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 8፡15

6. ደም መጣጭ መጋቢ እያስለቀሰህ ባሪያዎችህንና ከብቶችህን ይወስዳል። ደም መጣጭ መጋቢዎች አባሎቻቸው ያላቸውን ሀብት በስግብግብ አይን ይስልላሉ! የሀብታም አባሎቻቸውን ጥቅማ ጥቅምና ብልጽግና ይመኛሉ። ውድ መጋቢ ሆይ፣ አባላቶችህ በብዙ ድካም ያፈሩትን ሀብት ለአንተ እንደሚሰጡህ ተስፋ በማድረግ የምትመለከታቸው በደም መጣጭ መጋቢ አይን ይሆንን?

"ሎሌዎቻችሁንና ገረዶቻችሁን፥ ከከብቶቻችሁና ከአህዮቻችሁም መልካም መልካሞቹን ወስዶ ያሠራቸዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 8፡16

7. ደም መጣጭ መጋቢ እያስለቀሰህ ከበጎችህ አሥራትን ይወስዳል። ማህበሩ ሁሉ ‹‹ በቃ! በቃ! ከዚህ በላይ መስጠት አንችልም›› ብለው እስኪያለቅሱ ድረስ መባ ትሰበስባለህን? በምላሹ ለበጎችህ የምትሰጠው ነገር አለህን? በአመራርህ እስኪራቆቱ ድረስ ከአባላቶችህ ብዙ ትሰበስባለህን?

የአፍሪካ አገሮች እንደዚህ ባሉ ‹‹ውሰድ፣ውሰድ፣ውሰድ›› የሚል አስተሳሰብ ባላቸው ርዕሰ ብሄሮቻቸው ተራቁተዋል። የእነሱ ‹‹ዝረፍ›› አስተሳሰብ አፍሪካን ወደ ምድረ በዳነትና የጦርነት አውድማነት ቀይሯታል።

"ከበጎቻችሁና ከፍየሎቻችሁ አሥራት ይወስዳል፤ እናንተም ባሪያዎች ትሆኑታላችሁ። በዚያም ቀን ለእናንተ ከመረጣችሁት ከንጉሣችሁ የተነሣ ትጮኻላችሁ በዚያም ቀን እግዚአብሔር አይሰማችሁም። ሕዝቡ ግን የሳሙኤልን ነገር ይሰማ ዘንድ እንቢ አለ። እንዲህ አይሁን፥ ነገር ግን ንጉሥ ይሁንልን፥ እኛም ደግሞ እንደ አሕዛብ ሁሉ እንሆናለን። ንጉሣችንም ይፈርድልናል፥ በፊታችንም ወጥቶ ስለእኛ ይዋጋል አሉት። ሳሙኤልም የሕዝቡን ቃል ሁሉ ሰማ፥ ለእግዚአብሔርም ተናገረ።

1ኛ ሳሙኤል 8:17-21

## ሦስት የአገልጋይ መጋቢ አይነቶች

መጋቢዎች እግዚአብሔር በአደራ በሰጣቸው ህዝብ ላይ መሰልጠን ሳይሆን ሊያገለግሏቸው ይገባል። የሚያሳዝነው ግን የብዙ መሪዎች መከፈስ ከክርስቶስ ሀሳብ ጋር በአያሌው የሚለያይ መሆኑ ነው። እስከ አሁን ስለሌላኛው አይነት እረኛ ማለትም ስለ አገልጋይ እረኛ እንነጋገር። የአገልጋይነት ልብ ያላቸው መጋቢዎች ለህዝቡ ይሰጣሉ እንጂ ከህዝቡ አይነጥቁም። ሶስት አይነት አገልጋይ መጋቢዎችን እንደሚከተለው እገልጻለሁ።

1. በቤታቸው ተቀብለው የሚያስተናግዱ መጋቢዎች፡- በግሪክ ቋንቋ የዚህ ዓይነቱ መጋቢዎች ‹‹ዲያኮኒአ›› መጋቢዎች። ትርጓሜውም ሌሎችን የሚጠብቁ ወይም እንደ እንግዳ ተቀባይ፣ እንደ ወዳጅ ወይም እንደ መምህር የሚያገለግሉ ማለት ነው። እነዚህ መጋቢዎች ከሁሉ አስቀድመው በቤታቸው የሚቀበሉት እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔር ሌሎችን የመቀበል አገልግሎት ሊሰጥህ ይችላል። በጣም የከበረ አገልግሎት ስለሆነ

ልታቃልለው አይገባም፡፡ ማርታ ለዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ጥሩ ምሳሌ ነበረች፡፡

"በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ። ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ባች፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።"

ዮሐንስ 12፡2-3

2. ድጋፍ ሰጪ መጋቢዎች፡- የዚህ ዓይነቱ መጋቢዎች ድጋፍና አገልግሎትን ለሌሎች የሚሰጡ ናቸው፡፡ ብዙ መጋቢዎች ሌላውን ሰው እንዲደግፉ ተጠርተዋል፡፡ ሌሎችን እንዲደግፍ የተጠራን ሰው የቤተክርስቲያን ዋና መሪ ማድረግ ከፍተኛ ጥፋት ነው፡፡ ብዙ ‹‹ለመምራት የተጠሩ መሪዎች›› ጥሩ ድጋፍ ሰጪ ላይሆኑ ይችላሉ፤ እንዲሁም ጥሩ ድጋፍ ሰጪ አገልጋዮች በመምራት ጥሩ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ የመደገፍን አገልግሎት አታቃልል፡፡ ይህ የአገልጋይ መጋቢ ጥሪ ነው፡፡

«ሥራህንና ፍቅርህን፣ እምነትህንም፣ አገልግሎትህንም፣ ትዕግሥትህንም፤ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።»

ራእይ 2፡19

"ወይስ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ደመወዝ ስለ ሰበክሁላችሁ፥ እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን እያዋረድሁ ኃጢአት አድርጌ ይሆንን? እናንተን ለማገልገል ደመወዝ እየተቀበልሁ ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት ዘረፍሁ።"

2ኛ ቆሮንቶስ 11፡7-8

3. ከመድረክ ጀርባ የሚያገለግሉ መጋቢዎች፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ የተላላኪነት አገልግሎት የሚመስል ዝቅተኛ ሥራ የሚሰሩ መጋቢዎች አሉ፡፡ ዝቅተኛ የሚባሉ አገልግሎቶችን ለማገልገል አትፈር፡፡ ዝቅተኛ የሚባሉ ሥራዎች በእርግጥም አገልግሎቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነቱን ሥራ ማቃለል አገልግሎትህን ማቃለል ነው፡፡

«የተወደደ ወንድምና የታመነ አገልጋይ በጌታም አብሮኝ ባሪያ የሆነ ቲኪቆስ ኑሮዬን ሁሉ ያስታውቃችኋል።»

ቆላስይስ 4፡7

## ምዕራፍ 26

# የያህዌ የእረኝነት ጥበብ

እንደ እረኛ የተገለጸው ኢየሱስ ብቻ አለመሆኑን ስረዳ በመገረም ተደሰትኩ። ያህዌም ራሱን እንደ እረኛ ይገልጻል! በብሉይ ኪዳን በሙሉ ያህዌ በጎቹን ለመንከባከብ የሚተጋ እረኛ አድርጎ ራሱን ይገልጻል። ከያህዌ ከራሱ ሌላ ልንማርበት የምንችል ምን ሌላ የተሻለ ምሳሌ ይኖራል? እስኪ የመልካም እረኛን ተግባር ያሳየበትን የሁሉን ቻዩን ጌታ አንዳንድ ተግባራት እንመልከት፤

## ያህዌ የእረኝትን ጥበብ ያሳየባቸው አሥራ አምስት መንገዶች

### 1. ታላቁ እረኛ ያህዌ የጠፉትን በጎች ይፈልጋል

«ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ፤ እፈልግማለሁ። እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ። በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ፤ ከአገሮችም እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደገዛ አገራቸውም አመጣቸዋለሁ፤ በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡11-13

### 2. ታላቁ እረኛ ያህዌ በቀንበር ውስጥ ያሉትን በጎች ነጻ ያወጣል።

«እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ። በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡12

### 3. ታላቁ እረኛ ያህዌ የተበተኑትን በጎች ይሰበስባል።

«እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ፤ በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ፤ ከአገሮችም እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደገዛ አገራቸውም

አመጣቸዋለሁ፤ በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡12-13

## 4. ታላቁ እረኛ ያህዌ የተራቡትን በጎች ይመግባል፡፡

«በመልካሙ ስፍራ አሰማራቸዋለሁ፤ የእስራኤል ተራሮች ከፍታም የግጦሽ መሬት ይሆንላቸዋል፡፡ በመልካሙ ግጦሽ መሬት ይተኛሉ፤ እዚያም በእስራኤል ተራሮች ለምለም መስክ ላይይመገባሉ፡፡ እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ፤ አስመስጋቸዋለሁም፡፡ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡»

ሕዝቅኤል 34፡14-15 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## 5. ታላቁ እረኛ ያህዌ ለተቅበዘበዙ በጎች እረፍትን ይሰጣል፡፡

«በመልካሙ ስፍራ አሰማራቸዋለሁ፤ የእስራኤል ተራሮች ከፍታም የግጦሽ መሬት ይሆንላቸዋል፡፡ በመልካሙ ግጦሽ መሬት ይተኛሉ፤ እዚያም በእስራኤል ተራሮች ለምለም መስክ ላይ ይመገባሉ፡፡ እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ፤ አስመስጋቸዋለሁም፡፡ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡»

ሕዝቅኤል 34፡14-15 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## 6. ታላቁ እረኛ ያህዌ የተሰበሩትን በጎች ይጠግናል፡፡

«የጠፋውንም እፈልጋለሁ፤ የባዘነውንም እመልሳለሁ፤ የተሰበረውንም እጠግናለሁ፤ የደከመውንም አጸናለሁ፤ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ፤ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡16

## 7. ታላቁ እረኛ ያህዌ የደከሙትን በጎች ያጸናል፡፡

«የጠፋውንም እፈልጋለሁ፤ የባዘነውንም እመልሳለሁ፤ የተሰበረውንም እጠግናለሁ፤ የደከመውንም አጸናለሁ፤ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ፤ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡16

## 8. ታላቁ እረኛ ያህዌ ግራ የገባቸውን በጎች ይመራል፡፡

«ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ፤ እፈልግማለሁ። እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ፡፡ በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ፤ ከአገሮችም እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደገዛ

አገራቸውም አመጣቸዋለሁ፤ በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ።»

ሕዝቅኤል 34፡11-13

## 9. ታላቁ እረኛ ያህዌ የተሰበሩትን በጎች ይሸከማል።

«እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል፤ ክንዱም ስለእርሱ ይገዛል፤ እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው። መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።»

ኢሳይያስ 40፡10-11

## 10. ታላቁ እረኛ ያህዌ በጎቹ ምንም እንዳይጎድባቸው ያደርጋል።

«እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።»

መዝሙር 23፡1

## 11. ታላቁ እረኛ ያህዌ የዛሉትን በጎች ነፍስ ይመልሳል።

«እግዚአብሔር እረኛዬነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።»

መዝሙር 23፡1-3

## 12. ታላቁ እረኛ ያህዌ በጎቹን በጽድቅ መንገድ ይመራል።

"ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።"

መዝሙር 23፡3

## 13. ታላቁ እረኛ ያህዌ በፍርሃት ለተያዙት በጎች በጠላቶቻቸው ፊት ለፊት ገበታን ያዘጋጅላቸዋል።

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥የሚያሳጣኝም የለም።..."
"በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤ በጠላቶቼ ፊትለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።»

መዝሙር 23፡1፣5

## 14. ታላቁ እረኛ ያህዌ የተፍገመገሙትን በጎች ያጽናናል።

«በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፣ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።»

መዝሙር 23፡4

## 15. ታላቁ እረኛ ያህዌ ችግረኞችን በጎች ይቀባል።

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።..."

"በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።"

መዝሙር 23፡1፣5

## ምዕራፍ 27

# መልካም እረኛ ለመሆን የሚረዱ ሠላሳ አምስት ቁልፍ ነገሮች

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"

ዮሐንስ 10፡11

1. *"የመልካሙን እረኛ" ምሳሌነት በመከተል መልካም እረኛ ሁን። ኢየሱስ መልካም እረኛ ነበር።* ከኛ ማንም መልካም እረኛ ወይም መጋቢ ለመሆን የሚመኝ በቀጥታ ከእርሱ ሊማር ይገባዋል። በዚህ ምዕራፍ ስለ መልካሙ እረኛ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ባህሪ ትማራለህ። የእርሱን ምሣሌነት ከተከተልህ መልካም የቤተክርስቲያን መጋቢ ትሆናለህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍተኛውን መስኪያ አስቀምጦልናል። ከክርስቶስ ምሳሌነት የላቀ ምሳሌ አያስፈልገንም።

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"

ዮሐንስ 10፡11

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥... የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል።"

ዮሐንስ 10፡14

2. *በመስበክ፣ በማስተማር እና በመፈወስ መልካም እረኛ ሁን።*

"ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።"

ማቴዎስ 9፡35

3. *ከበጎችህ ጋር ህብረት በማድረግ መልካም እረኛ ሁን።* እያንዳንዱ እረኛ ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርግበትን ጥበብ ለይቶ ማወቅ አለበት። በሰዎች ላይ መልካም ተጽዕኖ ማምጣት አንድ መጋቢ ሊያሳድገው የሚገባ ክህሎት ነው። ከሰዎች ጋር መስራት ውስብስብ ጉዳይ ነው። ከሰዎች ጋር እንዴት ግንኙነት ማድረግ እንዳለብንና በእነርሱ ላይ ተጽዕኖን

እንዴት እንደምናመጣ መማር የልብ ቀዶ ህክምና ከማድረግ ይልቅ የሚከብድ ነው። ብዙ መጋቢዎች ይህን አስፈላጊ ነገር ሳይማሩ እንደኖሩና እንደሞቱ ተረድቻለሁ።

"ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።"

ዮሐንስ 10:3

4. *ወደ በጎች ጋጣ እንደ ሌባና ወንበዴ የሚገቡትን በመዋጋት መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ እርሱ የገነባውን ለማፍረስ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ አለበት። ጠላቶች የሕይወት አንድ አካል ናቸው። እግዚአብሔር ለዳዊት "ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ" አለው። ዳዊት ስለሚዋጋው ውጊያ በሚገባ የሚያውቅ ነበር። የክፋት እውንነትን የተረዳ ሰው ነበር። ከሁሉ ሰው ጋር በሠላም የሚኖር መልካምና ጨዋ ሰው ለመሆን በመሞከር አቋም የሌለው ሰው እንዳትሆን ተጠንቀቅ። አንዳንድ ጊዜ እንደ መልካም እረኛ ጠላትህን ለይተህ አውቀህ ልትፋለመው ይገባል።

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤"

ዮሐንስ 10:1

5. *በጎችን ሊነጥቁ የሚሞክሩትን ሁሉ ለይተህ በማወቅና በማውገዝ መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ በጎቹን ለመበከል የሚፈልጉትን ሐሰተኛ እምነቶችንና ሐሰተኛ እረኞችን የሚቃወም ትምሕርት ማስተማር አለበት። መልካም እረኛ ልክ ኢየሱስ እንዳደረገው ሌቦችና ወንበዴዎችን ማጋለጥ አለበት። ኢየሱስ ከእርሱ በፊት የመጡት ሌቦችና ወንበዴዎች እንደነበሩ አስተማረ። በጎችህ ሌቦችንና ወንበዴዎችን እንዴት ሊለዩ እንደሚችሉ አስተምራቸው።

"ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም።"

ዮሐንስ 10:8

6. *ለበጎችህ ጋጣን በማዘጋጀት መልካም እረኛ ሁን፡፡* መልካም እረኛ ለበጎቹ አስተማማኝ ቤት ያዘጋጃል፡፡ ይህ ሥጋት የሌለበት መኖሪያ ጋጣ ይባላል፡፡ መልካም እረኛ በጎቹን ያለ ችግር እንዲንከባከብ የሚያስችለው የቤተክርስቲያን ህንጻ ይገነባል፡፡ እያንዳንዱ መልካም እረኛ ለበጎቹ የማምለኪያ ቦታ ለመገንባት መሞከር አለበት፡፡

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤"

ዮሐንስ 10፡1

7. *መልካም መሪ በመሆን መልካም እረኛ ሁን፡፡* "የመምራት ጥበብ" በሚል ርዕስ በተለይ ለቤተክርስቲያን መጋቢዎችና እረኞች የሚሆን መጽሐፍ ጽፌአለሁ፡፡ መልካም እረኛ እንድትሆን ከሚያደርጉህ ነገሮች አንዱ ጠንካራና ውጤታማ መሪ የመሆን ብቃትህ ነው፡፡ መሪነት መጋቢዎች ሁሉ ሊማሩትና ሊያጠኑት የሚገባ ነገር ነው፡፡ መሪነት በትምሕርት ሊቀሰም የሚችል ሳይንሳዊ እውቀት ነው፡፡ የመሪነት እውቀት ሃያ ሰው ከመምራት አልፈህ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ መምራት የሚያሻግርህ አንዱ ነገር ነው፡፡

"ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል። የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤»

ዮሐንስ 10፡3-4

8. *ወደ በጎች በረት በትክክለኛው በር በመግባት መልካም እረኛ ሁን፡፡* ወደ በጎች በረት ህጋዊ በሆነ መንገድ የማትገባ ከሆንክ ስኬታማ እረኛ ልትሆን አትችልም፡፡ ብዙ እረኞች በኃላፊነት ቦታ ላይ የሚቀመጡት አግባብነት በሌለው መንገድ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ከሌሎች ቤተእምነቶች በጎችን የሚሰረቁ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የራሳቸውን ሚኒስትሪ ለማቋቋም ብለው ቤተክርስቲያንን ያፈርሳሉ፡፡ አንዳንድ እረኞች ሲያለግሉበት ለነበረው ቤተክርስቲያን ጥፋት ምክንያት ሆነዋል፡፡ አንዳንዶቹ ረዳት መጋቢዎች ሆነው ከቆዩ በኋላ የተወሰኑትን አባላት ከፍለው በመውሰድ ወጥተዋል፡፡ በሰረቁት ውሃ ህይወታቸውንና አገልግሎታቸውን ለማሳደግ ይጠቀሙበታል፡፡ መልካም እረኛ

ግን የራሱን ሚኒስትሪ የሚጀምረው (ወደ በጎች በረት የሚገባው) በትክክለኛው መንገድ ነው፡፡ ጅማሬ ወሳኝ ነው! ጅማሬዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው! መሠረትህ የምትሄድበትን ርቀትና የምታከናውነውን ነገር መጠኑን ይወስናል፡፡ "መሠረቱ ከተናደ፣ ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?" (መዝሙር 11:3)፡፡

"በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው።"

ዮሐንስ 10፡2

9. *የበረት ጠባቂው በሩን እንዲከፍትልህ በማድረግ መልካም እረኛ ሁን፡፡* መልካም እረኛ ለመሆን ከበር ጠባቂው ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ መልካም እረኛ ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት አለው፡፡ ከዋናው መሪ እንጂ ከሌሎች መሪዎች ጋር ግንኙነት የማያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡ መልካም እረኛ ራዕዩን ለማሳካት ጉድለቱን የሚሞላ የሌሎች ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ያምናል፡፡ እረኛው ወደ በጎች በረት ገብቶ አገልግሎቱን እንዲጀምር በር ጠባቂው ሊከፍትለት ያስፈልጋል፡፡ ከሞላ ጎደል የሁሉም አገልጋዮች ስኬት በሚያገኙት የሌሎች ድጋፍ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተምሬአለሁ፡፡

"በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው። ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።»

ዮሐንስ 10፡2-3

10. *ለበጎችህ መንፈሳዊ እይታን በማካፈል መልካም እረኛ ሁን፡፡* እረኛ በሁሉም መስክ ከበጎቹ አንድ እርምጃ ቀደም የሚል መሆን አለበት፡፡ ለበጎችህ የምታካፍለው ዕውቀትና ጥበብ ሊኖረህ ይገባል፡፡ ለማንበብና ዕውቀት ለማዳበር ጊዜ የሌለው እረኛ መልካም መጋቢ ሊሆን አይችልም፡፡ በምትመራቸው ሰዎች ላይ የሚኖርህ ሥልጣን እነርሱ ካላቸው በላይ ዕውቀትንና ጥበብን በመመገብ ብቃትህ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

"ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤እነርሱ ግን የነገራቸው ምን እንደሆነ አላስተዋሉም።"

ዮሐንስ 10፡6

11. በጎችህ ድምጽህን እንዲለዩ በማድረግ መልካም እረኛ ሁን። "በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤" (ዮሐንስ 10፡4)

አንዳንድ መጋቢዎች መድረኮቻቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለሌሎችም ስለሚፈቅዱ ብዙ እሁዶች ሲሰብኩ አይታዩም። ይህን የሚያደርጉት በትህትና በፍትህአዊነት ሰበብ ነው። አንዳንድ መጋቢዎች ከናካቴው በተለያየ ምክንያት ከእሁድ ውጭ ባሉ ፕሮግራሞቻቸውም የሚሰብኩት አልፎ አልፎ ነው። ይህ ላለመስበክ የሚሰጡ "የትህትና" ምክንያቶች በጎቹ የእረኛቸውን ድምጽ ሳያቋርጡ እንዳይሰሙ ያደርጋቸዋል። በዚህም ምክንያት የእረኛቸውን ድምጽ ለመለየት ይቸገራሉ።

በጎችህ ድምጽህን ከለመዱት ድምጽህን መለየት ይችላሉ! ድምጽህን በተደጋጋሚ ከሰሙት ድምጽህን ይለምዱታል። ለዚህ ነው ለበጎችህ አብዝተህ የእግዚአብሔርን ቃል መልዕክት ልታካፍላቸው የሚገባህ። በጎች ድምጽህን መለየት ያስፈልጋቸዋል። ድምጽህን ከለመዱት በአስቸጋሪ የህይወት ምዕራፍ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ድምጽህ የሚያጽናና ድምጽ ይሆንላቸዋል። በጎችህ ድምጽህን በሚያውቁበት ጊዜ ውሳኔ በሚጠይቅ በወሳኝ የህይወት ደረጃ ላይ ሲሆኑ የሚታዘዙት የአንተን ድምጽ ይሆናል። በህይወታቸው ከሚሰሟቸው የተለያዩ ድምጾች መካከል ያንተ ድምጽ ብቻ የሚታመን ይሆንላቸዋል።

"...በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፤ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።"

ዮሐንስ 10፡3

"በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ..."

ዮሐንስ 10፡27

12. *በጎችህን በስማቸው በማወቅ መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ የበጎቹን ስም ማወቅ አለበት። ከቤተክርስቲያን መጋዎች ተግባር አንዱ የእያንዳንዱን የቤተክርስቲያን አባል ስም ማጥናት ነው። የእያንዳንዱን ስም ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለብህ። ማንም ሰው ስሙን ካለወቅህ ደስ አይሰኝም። ማንም በቁጨት እንዲጠራ ወይም በችግሩ እንዲታወቅ አይፈልግም።

ብዙ ጊዜ የሰዎች ስም ይረሳና ችግራቸው መጠሪያቸው ይሆናል። ለምሳሌ መጋቢው "ያቺን የደም መፍሰስ ችግር

ያለባትን ሴት ጥሩልኝ" ወይም "ባለፈው ሳምንት ልጇ የሞተባት ሴት የታለች?" ወይም ደግሞ "ያ ጫጨቶቹን ድመት የበላበት ወንድም እንዴት ሆነ?" ሊል ይችላል፡፡

ከዚህም ሌላ ማንም ሰው በተቀጽላ ወይም "ፎቅ ላይ የሚኖሩት ሰዎች" ወይም "የውጭ አገር ዜጎቹ" በሚሉ ስሞች ሲጠራ ደስተኛ አይሆንም፡፡ የአባሎችህን ስም አጥና በዚያ ምክንያት ብቻ እንኳ አንተን መውደድ ይጀምራሉ፡፡

"...የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።"

ዮሐንስ 10፡3

13. *በጎችህን ወደ ለመለመ መስክ በመምራት መልካም እረኛ ሁን፡፡* መልካም እረኛ ለበጎቹ በቂ ምግብ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ አንዳንዴ ሁሉንም በጎች አንተ ልትመግባቸው አትችል ይሆናል፤ ነገር ግን መልካም ምግብ የሚያገኙበትን ሁኔቴ ማመቻቸት አለብህ፡፡ መልካም እረኛ ሌሎች አገልጋዮች እንዲሰብኩና አባሎቻቸውን እንዲባርኩለት ይጋብዛል፡፡ ይህ የመልካም እረኛ ተግባር ነው፡፡ ወደለመለመ መስክ ይመራቸዋል፡፡

"የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።"

ዮሐንስ 10፡3

14. *በጎችህን ከፊት ሆነህ በመምራት መልካም እረኛ ሁን፡፡* መልካም እረኛ መሆን ከበጎች ፊት መሄድን ያካትታል፡፡ ሁሉም ሰው ሊከተለው የሚችለው መልካም ምሳሌ ይፈልጋል፡፡ ብዙ የህይወት መመሪያ መርሆዎችን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች አሉ፡፡ እውነታው ግን እነኚህን መርሆዎች በተግባር በመኖር ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች ጥቂት መሆናቸው ነው፡፡ በህይወትህ መሪ ሁን፡፡ በትዳርም መልካም ምሳሌ ሁን፡፡ ወደ ብልጽግና ቀዳሚ ሁን፡፡ ከበጎችህ ፊት ሂድ እነርሱም ይከተሉሀል፡፡

"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፡፡"

ዮሐንስ 10፡4

15. *በጎችህ እንዲከተሉህ በማድረግ መልካም እረኛ ሁን።* *መሪነት ሌሎች እንዲከተሉህ ማድረግን ያጠቃልላል።* አንተ የጸሎት ሰው ሆነህ በቤተክርስቲያን ያሉትን ሰዎች እንዲጸልዩ ማድረግ አትችል ይሆናል። አንተ ራስህን ለጌታ የሰዋህ ሆነህ ሌሎች ያንኑ እንዲያደርጉ ማድረግ አቅቶህ ይሆናል። ነገር ግን መልካም እረኛ ወደሚሄድበት ሁሉ በጎቹ እንዲከተሉት የሚያደርግ ነው።

አንድ ቀን በአገልግሎት ብዙ ነገሮችን ካከናወኑ የእግዚአብሔር ሰው ጋር ቆይታ አድርጌ ነበር። እኚህ ሰው ሚሲዮናዊ ሆነው ለጌታ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል። ነገር ግን "በጣም ትልቅ ከሆነው ቤተክርስቲያኔ ውስጥ ማንንም እንደኔ ሚሲዮናዊ ማድረግ አልቻልኩም።" በማለት አምነዋል።

እረኛ በጎቹ እንዲከተሉት የማይችልበትን ሁኔታ በማስብበት ጊዜ እጅግ አዝናለሁ።

**"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል"**

**ዮሐንስ 10፡4**

**"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፣ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኛማል።"**

**ዮሐንስ 10፡27**

16. *በጎችህ ድምጽህን እንዲለዩ በማድረግ መልካም እረኛ ሁን።* በበጎች እድገት ውስጥ የእረኛን ድምጽ መለየት ከፍተኛ ሚና አለው። አንድ ሰው ‹‹ ብዙ አብያተክርስቲያናትን ጎብኝቻለሁ። ሁሉም አንድ ናቸው። ቤተክርስቲያን ቤተክርስቲያን ነው። ሁሉም እግዚአብሔርን ነው የሚያመልኩት። ሁሉም ነገር አንድ ዓይነት ነው።›› የሚል አስተያየት ከሰጠ በእርግጥ ያ ሰው የየትኛውም ቤተክርስቲያን ታማኝ አባል እንዳልነበረና እረኛ ኖሮት እንደማያውቅ መረዳት ይቻላል። እውነተኛ በጎች የእረኛውን ድምጽ ከመለየታቸውም ሌላ ሁሉም አብያተክርስቲያናትም ሆኑ ሁሉም እረኞች አንድ አይነት እንዳልሆኑ የተረዱ ናቸው። እውነተኛ በጎች የተለያዩ እረኞች ድምጽ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ የተረዱ ናቸው።

"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል።"

ዮሐንስ 10፡4

17. *የበጎች በር በመሆን መልካም እረኛ ሁን።* በር መሆን ማለት በጎቹ ወደ ፊት እንዲራመዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ማለት ነው። መልካም እረኛ በጎቹ ወደተለያዩ የህይወት ዘርፎች እንዲገቡ ያደርጋል። መልካም እረኛ በጎቹ ወደ ትዳር እንዲገቡ በማስተማርና በማማከር መንገዶችን ያመቻቻል።

መልካም እረኛ አስፈላጊውን ትምህርትና ምሪት በመስጠት በጎቹ ወደ ብልጽግና እንዲገቡ ያደርጋል። መልካም እረኛ በጎቹ ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ ያደርጋል። በዚህ መልክ ነው እረኛ የበጎች በር የሚሆነው።

"ኢየሱስም ደግሞ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ።"

ዮሐንስ 10፡7

"በሩ እኔ ነኝ።"

ዮሐንስ 10፡9

18. *ለበጎችህ ደህንነትን በመስጠት መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ የጠፋውን በግ ፍለጋ ይሄዳል። የጠፉትን በጎች ፍለጋ መሄድ የወንጌል ሥርጭት ይባላል። መልካም እረኛ በወንጌል ሥርጭት ላይ በሚገባ መሳተፍ አለበት። መልካም እረኛ በአገልግሎቱ ሰዎች ደህንነትን እንዲቀበሉ ምክንያት ይሆናል። መልካም እረኛ አገልግሎቱ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣትና ቀጥሎም የመጋቢነት አገልግሎት በመስጠት ይጀምራል። በአንተ አገልግሎት በኩል ደህንነትን ያገኙትን ሰዎች በመጋቢነት በምታገለግልበት ወቅት ምን ያህል የተረጋጉና ለአንተ ታማኞች እንደሆኑ ትረዳለህ። አለመታደል ሆኖ ብዙ መጋቢዎች የወንጌል ሥርጭት ክህሎታቸው ስለጠፋባቸው ከሌላ ጉባዔ ምዕመናንን በማስኮብለል ቤተክርስቲያናቸው እንዲያድግ ያልማሉ።

"በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም፤ ይወጣልም፤ መሰማርያም ያገኛል።»

ዮሐንስ 10፡9

19. *ለበጎችህ ህይወትን በመስጠት መልካም እረኛ ሁን::* መልካም መጋቢ በጎቹ የተሻለ ህይወት እንዲለማመዱ ያደርጋል:: ጥበብና ማስተዋልን የሚሰጥ ትምህርት በጎች የተሻለ ህይወት እንዲመሩ ያደርጋል:: ያለ እረኞችና መጋቢዎች ድጋፍ በጎች መልካም ህይወት ሊመሩ አይችሉም::

«...እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።»

ዮሐንስ 10፡10

20. *ህይወትህን ለበጎች በመስጠት መልካም እረኛ ሁን::* የተሻለ ህይወት ከመስጠት በተጨማሪ መልካም እረኞች በጎቻቸው መልካም ኑሮ ይኖሩ ዘንድ ህይወታቸውን ስለበጎቹ ያኖራል:: ህይወቱን በጎቹ በጉዞአቸው እንዲዘልቁ እንደምሳሌ ይጠቀምበታል:: ለበጎቹ የተሻለ ህይወት በማሰብ ብዙ ነገሮቹን መስዋዕት ያደርጋል:: ብዙ መጋቢዎች ለሚያገለግሉት ህዝብ መስዋዕትነት አይከፍሉም፣ ነገር ግን የእረኝነት ደረጃ የሚለካው ለህዝቡ በሚከፍለው መስዋዕትነት ነው::

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"

ዮሐንስ 10፡11

"...ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ።"

ዮሐንስ 10፡15

"ነፍሴን ደግሞ እንዳነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል።"

ዮሐንስ 10፡17

21. *ከምንደኛነት የጸዳ በመሆን መልካም እረኛ ሁን::* ለምንደኛ በጎቹን በትኖ መሄድ ምንም አይደል:: እውነተኛ እረኛ ግን በጎቹን በቀላሉ አይተውም:: ቅጥረኛ ስላይደሉ ህይወታቸውን በሙሉ ለእረኝነት አገልግሎት የሰጡ ናቸው::

"እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ምንደኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ምንደኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ምንደኛው ይሸሻል።"

ዮሐንስ. 10፡ 12-13

22. *በበጎች ባለቤትነት ስሜት በማገልገል መልካም እረኛ ሁን::* ስለማንኛውም ነገር የባለቤትነት ስሜት ካለን ለዚያ ነገር

መለወጥ ምክንያት ይሆናል። ይህ ነው በአለም ዙሪያ እየተከናወነ ላለው የመንግሥት የንግድ ተቋማትን ወደ ግል የማዛወር እንቅስቃሴ ምክንያት የሆነው። በተወሰኑ ሰዎች ባለቤትነት ያልተያዘ ነገር ሁሉ ምንም ጥንቃቄ አይደረግለትም ወይም በሚገባ አይስተዳደርም። እግዚአብሔር እያንዳንዱ እረኛ በጎቹን ርህራሄ እንደሌለው ሞያተኛ ሳይሆን እንደ ባለቤት ሆኖ በፍቅርና በእንክብካቤ እንዲይዛቸው ይፈልጋል።

"እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል፤ በጎቹንም ይበትናቸዋል።"

ዮሐንስ 10:12

23. *በጎችህ በአደጋ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ በመንቃት መልካም እረኛ ሁን።* የማይወድህ ሰው ሊያጠፋህ በሚችል አደጋ ውስጥ እንኳ መሆንህን አይረዳልህም። ብዙ ሰዎች ስለራሳቸው ብቻ ነው የሚያስቡት። ሰዎች ካንተ ካንሰር ይልቅ የእነርሱ ራስምታት እንደሚያሳስባቸው ስትረዳ ትገረማለህ። መልካም እረኛ በጎቹ በጭንቀት ውስጥ ሲሆኑ ያውቃል። ቀላል የሚመስሉ ነገሮች እንኳ በመልካም እረኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ያለመታደል ሆኖ ሞያተኛ ግን በጎቹ እንኳ ሲሞቱ አያያቸውም።

"እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል፤ በጎቹንም ይበትናቸዋል።"

ዮሐንስ 10:12

24. *በመከራ ጊዜ ከበጎችህ ጋር በመሆን መልካም እረኛ ሁን።* መከራ እየከፋ ቢሄድ እንኳ እረኛ ከበጎቹ ጋር መሆን አለበት። እረኛ እስከ መቃብር ድረስ፣በሆስፒታል፣ በየትኛውም የህይወት አጋጣሚ፣ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ በሚሆኑበት ወይም በየትኛውም መከራ በሚከሰትበት ሥፍራ ሁሉ ለበጎቹ መገኘት አለበት። ክፉ እረኞች ከበጎቻቸው ገንዘብ ለመውሰድ በጎቻቸው ባለጠጋ ሲሆኑ ብቻ ነው የሚጎበኟቸው። መልካም እረኞች ግን በመከራም ጊዜ ከበጎቻቸው ጋር ናቸው።

"እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል፤ በጎቹንም ይበትናቸዋል።

ዮሐንስ 10:12

25. *በጎችህን በቅርብ በማወቅ መልካም እረኛ ሁን፡፡* ስለ መልካም እረኛ በተናገረበት ክፍል ኢየሱስ በጎችን ስለማወቅ ትኩረት ሲሰጥ እናየዋለን፡፡ ይህ በእረኛውና በበጎቹ መካከል የሚኖረው መተዋወቅ አብረው በቆዩ መጠን የበለጠ እየጠነከረና እየጠለቀ የሚመጣ ነው፡፡ መጋቢዎች በጎቻቸውን ለዓመታት ካገለገሉ በኋላ ስለበጎቻቸው የሚያስገርም ነገር ማወቅ በሚጀምሩበት ጊዜ ገና በጎቻቸውን እንዳላወቁዋቸው እየተረዱ ይመጣሉ፡፡ እያንዳንዱን በግ በጥልቀት ማወቅ ለትክክለኛ የመጋቢነት አገልግሎት ወሳኝ እንደሆነ ትረዳለህ፡፡

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤… የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤»

ዮሐንስ 10፡14

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል፡፡»

ዮሐንስ 10፡27

26. *በጎችህ እንዲያውቁህ በማድረግ መልካም እረኛ ሁን፡፡* እረኛቸውን ባወቁት መጠን የበጎች በራስ መተማመን ይጨምራል፡፡ ለህዝቡ ምስጢር በመሆን የመጋቢነት አገልግሎት ልትሰጣቸው አትችልም፡፡ በጎችህ በድልህ፣በሽንፈትህ፣ በሐዘንህና በደስታህ መካፈል ይፈልጋሉ፡፡ ይህን ማድረግህ ቅን እንደሆንክና ለቃልህ የታመንክ መሆንህን እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል፡፡

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤…የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል፡፡»

ዮሐንስ 10፡14

27. *እግዚአብሔር አብን በማወቅ መልካም እረኛ ሁን፡፡* መንፈሳዊ ጉልበትን ለማግኘት ከእግዚአብሔር አብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ ቁልፍ ነው፡፡ በሥውር ከህያው አምላክ ጋር በሚገናኝ ሰው ላይ የእግዚአብሔር መገኘት ያርፋል፡፡ እረኝነት መንፈሳዊ አገልግሎት በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት ያስፈልጋል፡፡

«አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው…ነፍሴንም ስለበጎች አኖራለሁ።»

ዮሐንስ 10፡15

28. *በእግዚአብሔር በመታወቅ መልካም እረኛ ሁን።* በእግዚአብሔር ፊት ግልጽና እውነተኛ መሆን ለመልካም እረኝነት የሚያስፈልግ መንፈሳዊ እድገት ነው። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው፤ ሆኖም ግን አንተም ወደ እርሱ ቀርበህ ነፍስህን በፊቱ ማፍሰስ ይኖርብሀል። ይህን በማድረግህ ወደ እግዚአብሔር ህልውና ትቀርባለህ። ወደ እግዚአብሔር ህልውና መቅረብ መልካም እረኛ ያደርግሀል።

«አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው፤ ነፍሴንም ስለበጎች አኖራለሁ።»

ዮሐንስ 10፡15

29. *በተለያዩ በረቶች በጎችን በማስቀመጥ መልካም እረኛ ሁን።* በተለያዩ በረቶች በጎችን ማርባት የተለመደ በእረኝነት ሥራ ውስጥ የሚታይ እድገት ነው። በእረኝነት አገልግሎት ታሪክህ ውስጥ በየሥፍራው አጥቢያዎችን ማቋቋም በጣም አስፈላጊ ነው። ቅርንጫፎችን ለመክፈት አትፍራ። አባላቶችህ በተለያየ ምክንያት ወደሌላ ሥፍራ መዛወራቸው አይቀርም። ስለሆነም በሚንቀሳቀሱበት ሥፍራ ሁሉ የሚያመልኩበት ሥፍራ ያገኙ ዘንድ በተለያዩ ሥፍራዎች አጥቢያዎችን መክፈት አለብህ።

"ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።"

ዮሐንስ 10፡16

30. *በወንጌል ሥርጭት ሌሎችን በጎች ወደ በረትህ በማስገባት መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ መሆን ማለት የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ማድረግ ማለት ነው። ይህ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መንጋውን እንዲጠብቅ አደራ የሰጠው ማሳሰቢያ ነው። ‹‹አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።›› (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡5)።

"ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።"

ዮሐንስ 10፡16

31. *በተለያየ በረት ውስጥ ያሉትን በጎችህን በአንድ ላይ በመሰብሰብ መልካም እረኛ ሁን።* ይህ የሚያመለክተው በየሥፍራው ባቋቋምካቸው አጥቢያዎች ውስጥ ያሉት አባሎች ድምጽህን መስማት ይችሉ ዘንድ እንደ አንድ መንጋ በየጊዜው መሰብሰብ እንዳለብህ ነው።

ከአንተ ጋር ግንኙነት ያላቸው አጥቢያዎች በተደጋጋሚ በአንድነት ተገናኝተው ድምጽህን መስማታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የአንተን ድምጽ ይሰሙ ዘንድ የዚህ ዓይነቱ መሰባሰብ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ይህን መሰባሰብ የሚቃወሙትን አጥብቀህ ልትፋለማቸው ይገባል።

"ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።"

ዮሐንስ 10፡16

32. *የመንጋው ዋና መሪ በመሆን መልካም እረኛ ሁን።* በአንድ እረኛ ሥር መሆናቸውን ማወቅ ለበጎች አስፈላጊ ነው። በአንድ መርከብ ላይ ሁለት ካፒቴኖች ሊኖሩ አይችልም። በአመራርህ ግርታ እንዲፈጠር አትፍቀድ። ሁሉም ሰው መሪው ማን እንደሆነ እርግጠኛ እንዲሆን አድርግ። በአንድ በረት አንድ እረኛ ብቻ መኖሩ ለአንድነታችንና ከአካሉ ግራ መጋባትን ለማስወገድ ያገለግላል።

"ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።"

ዮሐንስ 10፡16

33. *ነፍስህን ስለበጎችህ ካኖርክ በኋላ እንደገና በማንሳት መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ ስለ በጎቹ ዋጋ መክፈልን ብቻ ሳይሆን እንደ በግ እረኛነቱ የሚገባውን ጥቅም የሚቀበልም መሆን አለበት። ይህ ነፍሱን ስለበጎቹ ባኖረ ነገር ግን ደግሞ እንደገና ባነሳት በክርስቶስ ሕይወት በጉልህ ታይቷል። እነዚህ ሁለት ክስተቶች ፈጽሞ ተቃራኒ ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን ሁለቱም የየራሳቸው ጊዜና ወቅት አላቸው።

"ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል።"

ዮሐንስ 10፡17

34. *ሕይወትህን በራስህ ተነሳሽነትና በፈቃድህ በመስጠት መልካም እረኛ ሁን።* መልካም እረኛ መቼና ምን መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ እንዳለበት እስኪነገረው አይጠብቅም። መስዋዕት ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው፤ ሆኖም ግን በሁኔታዎች ተገደህ የምትሰዋው ነገር ጉልበት አይኖረውም።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚወስኑት በከፍተኛ በሽታ ከተመቱ በኋላ ነው። ከመታመማቸው በፊት ምንም ነገር ለመሰዋት አይፈልጉም። ነገር ግን አይቀሬው እየመጣ መሆኑን ሲረዱ ለጌታ ምንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ ይመስላሉ።

ነገር ግን አንድን ነገር ተገዶ በማድረግና በፈቃደኝነት በማድረግ መካከል ልዩነት መኖሩ ለማንም ግልጽ ነው። ጠመንጃ ተደቅኖብን ጌታን ማገልገል በፈቃደኝነት እርሱን ከማገልገል ፈጽሞ የተለየ ነው። ተገደህ በምታገለግልበት ወቅት ልትርሮጥ፣ ልትዘልና ልትስቅ ትችላለህ ነገር ግን ሳቅህ የውሸት እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው! ነፍስህን በፈቃድህና በነጻነት ስለበጎችህ ለማኖር ወስን። ይህን በወጣትነት ዘመንህ አድርገው። ጠንካራ ሳለህ አድርገው። ጤናማ ሳለህ አድርገው! እግዚአብሔር ሰው አይደለም። እውነተኛ ባልሆኑ ነገሮችና በውሸት ሲታለል አይችልም!

**"እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።"**

**ዮሐንስ 10፡18**

35. *የብዙዎችን ህይወት ለመማረክ የሚያስችል በውስጥህ ያለውን ኃይል በመረዳት መልካም እረኛ ሁን።* በተሰጠህ ኃላፊነት መልካም እረኛ ስትሆን እግዚአብሔር የበለጠ ሥልጣን ይሰጥሃል። ይህ የምትቀበለው ሥልጣን ብዙዎችን ወደ ህይወት ለማምጣት ወይም ወደ ሞት ለመምራት ልትጠቀምበት ትችላለህ። የተሰጠህን ሥልጣን በጥበብ ተጠቀም። እግዚአብሔር ስለሰጠህ ነገር ሁሉ ይጠይቅሀል።

**"እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።"**

**ዮሐንስ 10፡18**

# ምዕራፍ 28

# ከበጎችህ ጋር ሊኖረህ የሚገባ የተለያዩ ዓይነት ግንኙነቶች

መልካም እረኛ ለመሆን በጎችህ ከአንተ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት። ስለሆነም እንደ መልካም እረኛና መሪ ከሰዎች ጋር መልካምና ሁሉን አሳታፊ የሆነ ግንኙነት ሊኖረህ ይገባል። ውጤታማ ያልሆኑ መጋቢዎች ብዙ ጊዜ የጠበቀና ሁሉን አሳታፊ የሆነ ግንኙነት የመመስረት ብቃት ይጎድላቸዋል።

የአንድ መጋቢ ግንኙነት የመፍጠር ችሎታው የመጋቢነት አገልግሎቱን ምንነት ያስረዳል። አንዳንድ መጋቢዎች ቤተሰባዊነትን፣ ህብረትን ለመፍጠር የሚያስችል ግንኙነት የመመስረት በቂ የሆነ ችሎታ የላቸውም።

አንድ መጋቢ በአንድ ወቅት ከኔ ጋር የነበረውን ወዳጅነት ሲገልጽ ሰምቼዋለሁ።

‹‹ከዳግ ጋር ግንኙነት ነበረኝ።›› አለ።

ለመናገር የፈለገው ከኔ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረው ነው። እኔ ደግሞ ያን ያህል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለን ፈጽሞ አስቤ አላውቅም። እንዲያውም በኔ በኩል ግንኙነታችን ላይ ላዩን እንደነበረ ነው የሚሰማኝ።

በተለያዩ ኮንፍረንሶች ላይ እንዲሰብክ እጋብዘው እንደነበረ ነው እንጂ ከኔ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው ሰው አድርጌ አስቤ አላውቅም።

እንደምትመለከቱት ሁለታችንም ስለ ግንኙነት ያለን መረዳት ፈጽሞ የተለያየ ነበረ። አንዳችን ግንኙነታችን የጠበቀ እንደነበረ እናስብ ነበር አንዳችን ደግሞ እስከናካቴው ግንኙነት ያልነበረን ያህል ይሰማናል። እንደታሪካዊ ዳራችንና አመለካከታችን ስለግንኙነት ያለን መረዳት የተለያየ ነው። የምንለማመደው የተለያየ አይነት ግንኙነት በእርግጠኝነት በምንሰጠው አገልግሎት ላይ ይንጸባረቃል።

በመሰረቱ የግንኙነትህ ጥልቀት ስለ ግንኙነት ባለህ መረዳትና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። አንዳንድ ሰዎች ስለአንድ አይነት ግንኙነት ብቻ ነው የሚያውቁት። በጎቻቸው ሊካፈሉት ስለሚገባቸው ሌሎች የተለያዩ አይነት ግንኙነቶች አያውቁም፤ ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት የላቸውም።ሰ

አንዳንድ ሰዎች የጌታና ባሪያ ግንኙነት ብቻ ነው መመስረት የሚፈልጉት፤ ምክንያቱም በህይወት ዘመናቸው የሚያውቁት የዛን አይነት ግንኙነት ብቻ ነው። አንዳንድ ወንዶች ስለወንድና ሴት ግንኙነት ከተነሳ የሚገባቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ነው።

አንዳንዶች ከሌሎች ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ግልጽና ነጻ ስላይደሉ የጠለቀ ግንኙነት መመስረት አይችሉም። እንዲህ ያሉ ሰዎች በህይወታቸው ዙሪያ መጋረጃ ያደርጋሉ። አስተዳደጋችንና ያለፈ ልምዳችን የምንመሰርተውን የግንኙነት ዓይነት የመቅረጽ ከፍተኛ አቅም አለው። እስኪ ከበጎችህ ጋር ልትገነባ ስለምትችላቸው አሥራ ሁለት ዓይነት ግንኙነቶች ላከፍልህ ፦

## 1. ከበጎችህ ጋር «የቅርብ ወዳጅ» ግንኙነት ይኑርህ።

> **"እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊትለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር። ሙሴም ወደ ሰፈሩ ይመለስ ነበር። ነገር ግን ሎሌው ብላቴና የነዌ ልጅ ኢያሱ ከድንኳኑ አይለይም ነበር።"**
>
> **ዘጸአት 33፡11**

> **"የሕፃንነት ወዳጅዋን የምትተው፣ የአምላክዋንም ቃልኪዳን የምትረሳ..."**
>
> **ምሳሌ 2፡17**

«ባልንጀራ» የሚለው ቃል በእብራይስጥ «ሪአ» (rea) ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ተባባሪ፣የቅርብ፣ወንድም፣አጋር፣አብሮ አደግ ወይም ጎረቤት የሚል ትርጉም አለው። መጋቢዎች ከበጎቻቸው ጋር የቅርብና ጥልቅ ግንኙነት ያስፈልጋቸዋል።

በጎች መጠበቅ በዕብራይስጥ ራሀ (ra'ah) የሚባል ሲሆን ትርጓሜውም ከአንድ ሰው ጋር እንደወዳጅ ህብረት ማድረግ ማለት ነው። ለምናገለግላቸው ሰዎች ጓደኛ መሆን የመጋቢነት አገልግሎት አካል ነው። ከሰዎች ጋር ጓደኝነት ስትመሰርት ወደ ህይወታቸው መግቢያ በር አገኘህ ማለት ነው።

ለውጤታማ የመጋቢነት አገልግሎት ከምታገለግላቸው ሰዎች ጋር ኑሮአቸውን የሚያጣቅልል ጥልቅ ግንኙነት መገንባት ያስፈልግሀል፡ ፡ ውጤታማ የሆነ የመጋቢነት አገልግሎት ይኖርህ ዘንድ በሰዎች የግል ጉዳይ ውስጥ መግባት መቻል አለብህ።

ለነገሩ እረኛ ችግር መፍታት ነው ተግባሩ፤ ታዲያ ሰዎች ችግራቸውን ካልተናገሩ እረኛው ይህን ተግባሩን እንዴት መፈጸም ይችላል?

የጠለቀ ግንኙነት በማይኖርበት ጊዜ በግራ መጋባት ዓለም ውስጥ መሆን ትጀምራለህ። ሠላም ሳይሆን ሁሉም ሠላም ነው ትላለህ። ፈጽሞ የማታውቃቸውን ሰዎች እንደምታውቃቸው ታስባለህ። ሰዎች ችግራቸውን አውጥተው ስላልተናገሩ ብቻ ምንም ችግር እንደሌለ ታስባለህ! የጠለቀ ግንኙነት ከሌለህ ለመጋቢነት ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ማስተዋል ታጣለህ። የጠለቀ ግንኙነት ከሌለህ ወደ ታላቅ ጉባኤ ሊያድግ የሚችል አነስተኛ የቤተሰብ ጉባኤ ከመመስረት ትገደባለህ።

የጠለቀ ግንኙነት አለመስረት ከሚያስከትላቸው አደጋዎች ታማኝ ያልሆኑ ሰዎችን ሴራ ለመለየት አለመቻል አንዱ ነው። ግንኙነትህ ላይ ላዩን ስለሆነ ሰዎች አንተን መጥላት መጀመራቸውን ወይም አንተን ማመን ማቆማቸውን አታውቅም። በሰዎች የለበጣ ትህትና አትታለል። ትህትናንና መልካም ባህሪን ማሳየት ታማኝነትን ሊተኩ አይችሉም።

አብረውት ያገለግሉ የነበሩ ሰዎች በድንገት በካዱት ጊዜ ፍጹም በድጋጤ የተመታን አንድ መጋቢ አስታውሳለሁ። ይህ ሰው ከሰዎች ጋር የተለመደ አይነት ግንኙነት የሚያደርግ ሰው ነበር። ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት በአብዛኛው ወደ ፕሮቶኮልና ወደ ሥርዓታዊ ግንኙነት ያዘነብል ነበር። በዚህም ምክንያት ጠበቅ ያለ ግንኙነት የማድረግ ችሎታ አልነበረውም።

ጥልቅ ግንኙነት ከማይታይባቸው የግንኙነት ዓይነቶች አንዱ በጓደኛሞች መካከል ያለው ግንኙነት ነው። መጋቢዎችና መሪዎች ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ጋር ከትህትናና ከፎረማሊቲ ያለፈ ጓደኝነት መመሥረት አለባቸው። ጓደኛህ በቀላሉ አይክድህም! እንደባሪያ ከሚያገለግልህ የአገልግሎት አጋርህ ይልቅ ጓደኛ የሚሆንህና

ከወንድም ይልቅ የሚጠጋህ የአገልግሎት አጋርህ አጠገብህ መገኘቱ የበለጠ አስተማማኝ ነው።

በጎቻቸውን ተሳታፊ ለማድረግ አገልጋዮች ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ጋር የጠበቀ ጓደኝነት መመስረት አለባቸው። በዋና መጋቢዎችና በረዳቶቻቸው መካከል የጠለቀ ግንኙነት ካለ ግንኙነታቸው የበለጠ ይጠናከራል። እውነተኛ ጓደኝነት ካለ በመጋቢውና በህዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት ይጠነክራል። ለህይወትህና ለአገልግሎትህ አስፈላ ከሆኑ ሰዎች ጋር ጠንካራ ጓደኝነት ይኑርህ።

## 2. ከበጎችህ ጋር ‹‹የአለቃና ምንዝር›› ግንኙነት ይኑርህ።

**"ከእናንተም የሚያርስ ወይም ከብትን የሚጠብቅ ባሪያ ያለው፥ ከእርሻ ሲመለስ ወዲያው ቅረብና በማዕድ ተቀመጥ የሚለው ማንነው? የምበላውን እራቴን አሰናዳልኝ፥ እስክበላና እስክጠጣ ድረስ ታጥቀህ አገልግለኝ፥ በኋላም አንተ ብላና ጠጣ የሚለው አይደለምን?"**

**ሉቃስ17፡7-8**

የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት በተፈጠረው ግንኙነት ውስጥ ትልቁ ከባሪያው ጋር ግንኙነት እንደሚያደርግ ጌታ የሚንቀሳቀስበት የግንኙነት ዓይነት ነው። የዚህ ዓይነት ግንኙነት የሥልጣን ተዋረድ እንዳይጣስ ወይም እንዳይቃለል ለማድረግ ይጠቅማል። እንዲህ ያለው ግንኙነት ‹‹ደረጃ›› እና ‹‹ልዩነት›› ላይ ያተኮረ ነው። ከላይ ካነበብነው ጥቅስ እንደምንረዳው ባሪያው ከጌታው ፈጽሞ የተለየ ህይወት ነው ያለው። ጌታው ሲያርፍ ባሪያ ግን በሥራ ይደክማል። በጌታና በባሪያ መካከል ሊኖር የሚችለውን ጉዳይ ሁሉ በማውሳት በመካከላቸው ያለው ልዩነት በግልጽ ተቀምጧል። የኃላፊነት ደረጃና ልዩነት ትኩረት በሚያገኙበት ጊዜ ተገቢ ሥርዓት ለመመስት ይጠቅማል። ችግሩ ግን ይህ ሥረዓትን ማስከበር ስውር የሆነን አለመታመን ማስቀረት አለማቻሉ ነው።

የጌታና ባሪያ ዓይነት ግንኙነት ከዚህም በተጨማሪ ፍርሀትን ሊወልድ ይችላል። ከሥራ እባረራለሁ ተደማጭነት አጣለሁ የሚሉ አይነት ፍርሀቶች ይፈራሉ። ተደማጭነት አጣለሁ የሚል ፍርሀት ሰዎች ግብዞችና አስመሳዮች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። የጌታና ባሪያ አይነት ግንኙነትን አብዝቶ በሚከተል መጋቢ ዙሪያ ፈጽሞ ለስርሱ ፍቅር የሌላቸው ግብዞች፣አስመሳዮችና ውሸታሞች ይሰበሰባሉ።

አገልጋይህ ስላንተ ምን እንደሚያስብ አታውቅም፡፡ አገልጋይህ ሊገድለህ ይፈልግ አይፈልግ አታውቅም፡፡ ከጓደኛህ ይልቅ አገልጋይህ ሊገድልህ እንደሚችል ማመን ይቀላል፡፡ ንጉሥ አሞጽና ንጉሥ ኢዮስያስ የተገደሉት በጓደኞቻቸው ሳይሆን በባሪያዎቻቸው ነው፡፡

> "አሞጽም መንገሥ በጀመረ ጊዜ የሀያ ሁለት ዓመት ጎልማሳ ነበረ፡፡ በኢየሩሳሌምም ሁለት ዓመት ነገሠ፤እናቱም የዮጥባ ሰው የሐሩስ ልጅ ሜሶላም ነበረች። አባቱም ምናሴ እንዳደረገ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠራ። አባቱም በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ፥ አባቱም ያመለካቸውን ጣዖታት አመለከ፤ ሰገደላቸውም። የአባቶቹንም አምላክ እግዚአብሔርን ተወ፥ በእግዚአብሔርም መንገድ አልሄደም። የአሞጽም ባሪያዎች አሴሩበት፤ንጉሡንም በቤቱ ውስጥ ገደሉት፡፡ የአገሩ ሕዝብ ግን በንጉሡ በአሞጽ ላይ ያሴሩበትን ሁሉ ገደሉ፤ የአገሩም ሕዝብ ልጁን ኢዮስያስን በእርሱ ፋንታ አነገሡት።"
>
> 1ኛ ነገሥት 21፡19-24

በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ንጉሥ ኢዮስያስ በባሪያዎቹ ሲገደል እንመለከታለን፡፡

> "እንዲሁም ንጉሡ ኢዮአስ ዮዳሄ ያደረገለትን ቸርነት አላሰበም፥ ልጁንም ዘካርያስን አስገደለው፤ እርሱም ሲሞት እግዚአብሔር ይሻው፥ ይፈልገውም አለ። ዓመቱም ካለፈ በኋላ የሶርያውያን ሠራዊት መጡበት፡፡ ወደ ይሁዳና ወደ ኢየሩሳሌምም መጥተው ከሕዝቡ መካከል የሕዝቡን አለቆች ሁሉ አጠፉ፥ ምርኮአቸውንም ሁሉ ወደ ንጉሡ ወደ ደማስቆ ላኩ። የሶርያውያንም ሠራዊት ቍጥር ጥቂት ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ታላቅን ሠራዊት አሳልፎ በእጃቸው ሰጣቸው፤ ይህም የሆነው የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ትተው ስለነበረ ነው። እነርሱም በኢዮአስ ላይ ፍርድ ፈረዱበት። ከእርሱም ዘንድ አልፈው ከሄዱ በኋላ እጅግ ታምሞ ነበር፤ የገዛ ባሪያዎቹም ስለ ካህኑ ስለ ዮዳሄ ልጅ ተበቅለው ተማማሉበት፥ በአልጋውም ላይ ገደሉት፥ሞተም፡፡ በዳዊት ከተማ እንጂ በነገሥታት መቃብር አልቀበሩትም። የተማማሉበትም የአሞናዊቱ የሰምዓት ልጅ ዛባድ፥ የሞዓባዊቱም የሰማሪት ልጅ ዮዛባት ነበሩ።"
>
> 2ኛ ዜና መዋዕል 24፡22-26

አንተ በቤተ መንግሥት ተቀምጠህ አገልጋዮችህን ወደ ታች እየተመለከትክ አንተን የሚቃወምህን እንዴት ለይተህ ማወቅ ትችላለህ? ጓደኛ ሳታደርጋቸው አገልጋዮችህ ምን እንደሚያስቡስ በምን ታውቃለህ? አገልጋዮቻቸው በጠላትነት ተነስተውባቸው ከገደሏቸው ነገሥታት አንዱ መሆን ትፈልጋለህን?

## 3. ከበጎችህ ጋር « የሙሽርና የሙሽሪት» አይነት ግንኙነት ይኑርህ፡፡

"ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል፤ ይንከባከበውማል።"

ኤፌሶን 5፡25-26

የሙሽራና ሙሽሪት አይነት ግንኙነት በጎችን ወደ አንተ የሚያቀርብ ማራኪ ግንኙነት ነው። ብዙ ጊዜ ማራኪነት ስለሌላኛው ሰው ለማወቅ በምንፈልገው ሚስጢር ላይ የተመሰረተ ነው። ሙሽራና ሙሽሪት በፍቅር የሚፈላለጉት በአብዛኛው ስለእርስ በእርሳቸው ብዙ የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ነው። በጊዜው የሚገለጠው የየራሳቸው ድብቅ ማንነት በመካከላቸው ደስታን ከመፍጠሩም በላይ እርስ በእርስ ያቀራኛቸዋል።

እያንዳንዱ የመጋቢነት ግንኙነት የተወሰነ ያህል የዚህ አይነቱ ማራኪነት በእርግጥ እንደሚያስፈልገው መናገር ይቻላል። አዲስ ነገር የሌለው ግንኙነት መነሳሳትን ያጠፋል። ማራኪነት የጎደለው ግንኙነት የማይረባና የማይጠቅምና አሰልቺ ሲሆን በጎችን ተሳታፊ ለማድረግ አያስችልም። ለበጎችህ በምትሰጠው አገልግሎት ደስተኛ መሆን አለብህ። በጎችህ ባያመሰግኑህ እንኳ እነርሱን ለመከታተል አቅምና ጉልበት ሊኖርህ ይገባል። ብዙ ጊዜ ወጣቶች የአገልግሎት ፍቅርና መነሳሳት ስላላቸው በሙሽራና ሙሽሪት ግንኙነት ላይ የተሻሉ ናቸው።

## 4. ከበጎችህ ጋር «የአባትና ልጅ» አይነት ግንኙነት ይኑርህ።

"ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው።"

ምሳሌ 1፡8

አንድ መጋቢ ከበጎቹ ጋር ሊኖረው የሚገባ ሌላው አይነት ግንኙነት የአባትና ልጅ ግንኙነት ነው። ይህ መጋቢው በጎቹን እንደ ልጅ እንዲንከባከብ የሚያስችለው ጥልቅ ግንኙነት ነው። ቤተሰብ ይመሰረታል መጋቢው ደግሞ አባት ለወንድና ሴት ልጆቹ እንደሚያደርገው ለበጎቹ የሚያስፈልገውን በማቅረብ በጎቹን ይንከባከባል።

ይህ ግንኙነት ፍቅር በተሞላበትና ዋስትናን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ማማከር፣ አቅጣጫ ማሳየትና ምሪትን የሚያካትት ነው። ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ከአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ይልቅ የጠነከረ ነው። የላቀ

መተማመንና መታዘዝ ያለበት በመሆን የጠለቀና ሊከናወን የሚችል ግንኙነት ነው፡፡

"ልጄ ሆይ፥ ስማ፥ ንግግሬንም ተቀበል፤የሕይወትህም ዘመን ትበዛልሃለች።"

ምሳሌ 4፡10

"ልጄ ሆይ፥ ንግግሬን አድምጥ፤ ወደ ቃሌም ጆሮህን አዘንብል።"

ምሳሌ 4፡20

"ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው፡፡"

ምሳሌ 6፡20

## 5. ከበጎችህ ጋር ‹‹የመምህርና ደቀ-መዝሙር›› አይነት ግንኙነት ይኑርህ፡፡

"ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ እርሱም፦ ጌታሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው።"

ዮሐንስ 13፡16

ይህ በርካታ ሥልጠናዎችን የሚያካትት የግንኙነት አይነት ነው፡፡ በቋሚነት ከሚሰጥ ትምህርትና ሥልጠና የተነሳ በህዝብ መከበርን ታገኛለህ፡፡ በጎችን የምታስተምር ከሆነ የማይታመን ሥልጣን ታገኛለህ፡፡

ለማስተማር ድፍረት ባገኙባቸው ጉዳዮች ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኖርሀል፡፡ ሰዎች ስለአንዳንድ ጉዳዮች የማያስተምሩበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች ስለአንዳንድ ጉዳዮች እውቀቱም ስለሌላቸው አስተያየት መስጠት እንኳ አይችሉም፡፡ አንዳንዴ መጋቢዎች ስለፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ እና ስለመሪነት ምንም እውቀት የላቸውም፤መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚያውቁ ነው የሚመስሉት፡፡

አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች ጋብቻን ስለሚመለከቱ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለማስተማር ያፍራሉ፡፡ በአንዳንድ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ስለማያስተምሩ ሥልጣናቸው ውሱን ይሆናል፡፡አንዳንድ መጋቢዎች ለረዳት አገልጋዮቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር የሚያስችላቸው አይነት ግንኙነት ለመመስረት አይችሉም፡፡ ሰዎችን ፊት ለፊት ማየት ስለማይደፍሩ በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ማስተማር ይከብዳቸዋል፡፡ ይህም ረዳቶቻቸውን መቆጣጠርና መምራት

የሚችሉበትን አቅም ይገድባል። ከምትመራቸው ሁሉ ጋር የመምህርና ደቀመዝሙር ግንኙነት መመሥረት በጣም ጠቃሚ ነው።

## 6. ከበጎችህ ጋር «የባልና ሚስት» ግንኙነት ይኑርህ።

"ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ።"

ኤፌሶን 5:25

ከበጎችህ ጋር «የባልና ሚስት» ግንኙነት ብዬ የምጠራውን አይነት ግንኙነት መመሥረት ትችላለህ። የዚህ አይነቱ ግንኙነት ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው። አብረህ ኖረህ አብረህ ለመሞት እስከምትወስን ድረስ ከሰዎች ጋር ቋሚ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነትን መመስረትን የሚያካትት ነው። የተሻለ ደሞዝ እስከምታገኝ ድረስ ለተወሰነ አመት በተቀጠርከው ቦታ ከሚኖርህ ግንኙነት ፈጽሞ የተለየ ነው።

የባልና ሚስት አይነት ግንኙነት በጣም ቤተሰባዊ የሆነ ግንኙነት ነው። የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት መመሥረት ስትችል ከህዝቡ ጋር በግል ጉዳያቸው ላይ ለመነጋገር ትችላለህ። ይህ አባሎችህን ወደ አንተ የሚያቀርባቸው ሲሆን ህይወታቸውን ከህይወትህ ጋር እንዲጣመር ያደርጋል። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ከመጠን ያለፈ እንዳይሆን ደግሞ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

## 7. ከበጎችህ ጋር «የራስና የቀሪው የሰውነት ክፍል» አይነት ግንኙነት ይኑርህ።

"እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።"

"እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።"

ቆላስይስ 1፡ 17-18

በራስና በቀሪው የሰውነት ክፍል መካከል ባለው ግንኙነት የራስ ውሳኔ ሰጪነትና መሪነት በቀሪው የሰውነት ክፍል ተቀባይነት ያገኛል።በእንዲህ አይነቱ ግንኙነት ውስጥ እረኛው የበጎቹን የአሁንና የወደፊት ህይወታቸውን የሚለውጥ ውሳኔ መወሰን ይጠበቅበታል። አንዳንድ መጋቢዎች የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ከመፍጠር ይልቅ በቤተክርስቲያናቸው የዲሞክራሲ ባህልን ያስፋፋሉ። ዲሞክራሲ ጥሩ

ነው፤ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ሊገድል ይችላል፡፡ ለፈጣን እድገት ጠቃሚ የሆነውን የራስና የቀሪው ሰውነት አይነት ግንኙነትንም ያጠፋል፡፡

ማህበሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ወደ ፊት ይራመድ ዘንድ ይህ አይነቱ ግንኙነት በእርግጥ አስፈላጊ ነው፡፡

## 8. ከበጎችህ ጋር ‹‹የቅርንጫፍና ግንድ›› አይነት ግንኙነት ይኑርህ፡፡

"እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና፤ በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።"

ዮሐንስ 15፡5

ቅርንጫፍ ግንድ ግንኙነት ወደ ከፍተኛ ፍሬ ማፍራት የሚመራ ጥልቅ የእርስ በእርስ ግንኙነት ያመለክታል፡፡ ቅርንጫፎች ከግንዱ ጋር ፍጹም በሚጣበቁበት ጊዜ ፍሬ ያፈራሉ፡፡ ይህ ቃልህ በቃሉ እንዲሁም መንገድህ በመንገዱ እስኪዋጥ ድረስ ከመሪህ ጋር የምትዋሀድበት መንገድ ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምርጥ የሆነውን ፍሬ ለማፍራት ዝግጁ ሆንክ ማለት ነው፡፡

ጥልቅ የእርስ በእርስ ግንኙነት ቅባትንና ሌሎችንም አስፈላጊ ነገሮችን መካፈልን ያስከትላል፡፡ ህይወትና ራዕይ በእርስ በእርሳቸው ውስጥ እስኪሰርጹ ድረስ የሚያደርስ ግንኙነት የመመሥረት ራዕይ ይኑርህ፡፡

## 9. ከበጎችህ ጋር ‹‹የወይን በታና የወይን በታ ባለቤት›› አይነት ግንኙነት ይኑርህ፡፡

"ለወይኔ ያላደረግሁለት፥ ከዚህ ሌላ አደርግለት ዘንድ የሚገባኝ ምንድርነው? ወይንን ያፈራል ብዬ ስተማመን ስለምን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ? አሁንም በወይኔ ላይ የማደርገውን እነግራችኋለሁ፤ አጥሩን እነቅላለሁ፥ ለማሰማርያም ይሆናል፡፡ ቅጥሩንም አፈርሳለሁ፥ ለመራገጫም ይሆናል። ባድማ አደርገዋለሁ፤ አይቈረጥም፥ አይኰተኰትም፤ ኵርንችትና እሾህ ይበቅልበታል፤ ዝናብንም እንዳያዘንቡበት ዳመናዎችን አዝዛለሁ።"

ኢሳይያስ 5፡4-6

ይህ ዓይነቱ ግንኙነት አንድ ሰው ፍሬያማ እስኪሆን ድረስ መንከባከብን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ፍሬያማነቱን የሚያግዱትን አላስፈላጊ ነገሮችን የመግረዝና የመቁረጥ ብቃትን ይመለከታል፡፡

የዚህ አይነቱ ግንኙነት ምንም እንኳ የሚያሳምም ቢሆንም የማያስፈልጉ ሰዎችን ማስወገድን ያካትታል፡፡

መልካም እረኛ ጠንካራ ህብረቶችን መገንባት አለበት፡፡ ጠንካራ ህብረት ለመመስረት ከሳሾችን፣ አጉረምራሚዎችን፣ ሀሜተኞችን ፣ ስም አጥፊዎችንና የማይረኩ ሰዎችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ የዚህ አይነቱን ‹‹የመጋቢነት ኃላፊነት›› የማትወጣ ከሆነ የቀሪዎቹን ተከታዮችህን ህይወት አደጋ ላይ ትጥላለህ፡፡ አንድ የበሰበሰን ፍሬ ቆርጠህ ባለመጣልህ ሌሎቹ ፍሬዎች እንዲበላሹ ታደርጋለህ፡፡

ታማኝነትን ማጉደል አፋጣኝ መፍትሄ ሊበጅለት የሚገባ መንፈሳዊ ጉዳይ ነው፡፡

## 10. ከበጎችህ ጋር ‹‹የሸክላና የሸክላ ሰሪ›› አይነት ግንኙነት ይኑርህ፡፡

"ይህ የእናንተ ጠማምነት ነው እንደ ሸክላ ሠሪ ጭቃ የምትቈጠሩ አይደላችሁምን? በውኑ ሥራ ሠሪውን፦ አልሠራኸኝም ይለዋልን? ወይስ የተደረገው አድራጊውን፦ አታስተውልም ይለዋልን?"

ኢሳይያስ 29፡16

በዚህ አይነቱ ግንኙነት ውስጥ መጋቢው ህዝቡን ለእግዚአብሔር የሚጠቅሙ ዕቃዎች አድርጎ ይቀርጻቸዋል፡፡ ሰዎችን መቅረጽ ከማስተማር የዘለለ ነው፡፡ የመምህር-ደቀመዝሙር ግንኙነት ማስተማርን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡ ነገር ግን የሸክላና የሸክላ ሰሪው አይነት ግንኙነት በእረኛው አማካይነት የሚሆን የአንድን ሰው ፈጽሞ መለወጥ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ አይነቱ ግንኙነት የበጎች መላ ህይወት ይለወጣል፡፡

ትምህርት የማግኘት ጉዳይ አይደለም፣ የሰው መላ ህይወት ወደ አንድ የተለየ መልክ መቀረጽን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጥቂት ትምህርቶችን ማስታወሻ እየያዙ ከመማር ያለፈ መሆኑን አንተም ትገነዘባህ፡፡ ቀድሞ ለሚያውቁህ ሰዎች እንግዳ እስከምትሆን ድረስ አንዳንድ አስገራሚ ነገሮችን ማድረግ ወደምትችልበት ህይወት ትለወጣህ፡፡ የዚህ አይነቱን ግንኙነት ለመመሥረትት አትፍራ፡፡

በአንድ የምሽት የቤተክርስቲያን አገልግሎት እጅ በመጫን ለሰዎች እጸልይ ነበር፡፡ በአንደኛው ሰው ላይ እጄን ስጭን ልቆጣጠረው

በማልቻል መልኩ ማልቀስ ጀመርኩ። በኋላም ለምን እንደዛ እንዳለቀስኩ ማሰብ ጀመርኩ። ወዲያው ግን የዚህ ሰው ህይወት ለዘላለም ተለውጧል የሚል ነገር ወደልቤ መጣ። ያ ግለሰብ ስብከት ለማዳመጥ ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ የህይወት ለውጦች ለማግኘት ነበር በዚያ ምሽት የመጣው። ለሚሲዮናዊነት አገልግሎት ለመውጣት በዝግጅት ላይ ስለነበረ በህይወቱ በሁሉም አቅጣጫ እየተለወጠ ነበር። ሸክላ ሰሪው ሸክላውን በሚያበጀው ጊዜ የሸክላው ሁለንተና ይቀየራል። ከበጎችህ ጋር የሸክላና የሸክላ ሰሪ ግንኙነት አይነት ግንኙነት ካለህ በበጎችህ ህይወት ፍጹም ለውጥን መጠበቅ ትችላለህ።

## 11. ከበጎችህ ጋር ‹‹የወታደርና የአዛዥ›› አይነት ግንኙነት ይኑርህ።

**እርሱም፦ አይደለሁም፤ እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድርነው? አለው። የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ ኢያሱን አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።**

**ኢያሱ 5፡14-15**

አንድ የጦር አዛዥ ከወታደሮቹ ጋር ያለው ግንኙነት አይነት አንተም ከበጎችህ ጋር ሊኖርህ ይችላል። የመጋቢነት አገልግሎትህ የተሟላ እንዲሆን የሚያስችል አስፈላጊ የሆነ ወታደራዊ የአመራር ስልት አለ። ቤተክርስቲያንህ ካደገች በኋላ አባሎችህን ወደ አለም ሁሉ ሂዱና ደቀመዝሙር አድርጉ ብለህ ማዘዝ መቻል አለብህ።

የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ለመፍጠር አባሎችህን ስለ መስዋዕትነት ማስተማር አለብህ። የመከላከያ ጦር ሞትን እንደውሀ መጠጣት የወሰኑ በከፍተኛ ዲሲፕሊን የታነጹ ሰዎች ያሉበት ኃይል ነው። ምዕመናን መስዋዕትነት ስለመክፈል ከተማሩ ያደርጉታል።

ለነገሩ ክርስትና የተመሰረተው ራስን መስዋዕት በማድረግ እውነት ላይ ነው። ‹‹ መስቀልህን ተሸክመህ ኢየሱስን ተከተል›› የሚለው ትዕዛዝ በቤተክርስቲያን ገኖ መሰማት አለበት። ‹‹የወታደርና አዛዥ›› ግንኙነት ሲመሰረት አንዱን ‹‹ሂድ›› ስትለው ይሄዳል፣ ሌላውን ደግሞ ‹‹ና›› ስትለው ይመጣል። አንተ ስላልክ ብቻ ህዝቡ ወደየትም እንዲሄዱ ወይም ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ መጠየቅ ትችላለህ።

## 12. ከበጎችህ ጋር «የፈጣሪና የፍጥረቱ» አይነት ግንኙነት ይኑርህ።

**"በውኑ ሥራ ሠሪውን፦ አልሠራኸኝም ይለዋልን? ወይስ የተደረገው አድራጊውን፦ አታስተውልም ይለዋልን?"**

**ኢሳይያስ 29፥16**

የዚህ አይነቱ የመጋቢነት ግንኙነት ከሸክላና ከሰሪው ግንኙነት ጋር ይመሳሰላል። ይህ በጥቅሉ ካልሆነ ነገር የሆነን ነገርን ስለማውጣት ነው። አንድ መጋቢ ካልታሰቡ ሰዎች ታላላቅ ሰዎችን በማውጣት የተካነ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ቅርጽ ከሌለው ባዶ ነገር ይህን ያማረ ምድር በፈጠረ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው። መጋቢዎች በተናቁ ሰዎች ውስጥ የከበረ ነገር ማየት አለባቸው። አንድ መጋቢ በቤተክርስቲያኑ እንዲህ ያሉ የተቀቡ ሰዎች ከሌሉ ብዙ ጊዜ ምክንያቱ በተናቁ ሰዎች ውስጥ ያለውን የከበረ ነገር ማየት ስላቃተው ነው። ጥሬ ዕቃዎችን ወስደህ ግብአቶችን ዋጋ ወዳላቸው ነገሮች የመለወጥን ጥበብ መማር ይኖርብሃል።